ታሪክ ፡ በቲያትር ፡ መልክ ።

# ዘርዓይ ፡ ደረስ ።



ተጻፈ ፡ ከአንተነህ ፡ ዓለሙ ፡

ዘብሔረ ፡ ጐጃም ፡

ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወፍኖተ ፡ ሰላም ።

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤ ቍ 1607

QQD
963.056
----------
160,275

$ 1¢25

~~S XIII Abyss. Amharic~~

QQD 963.056 ~~59~~

ANTANAH ALAMU

[Tārik ba-tiyāter malk. Zar'āy Daras.
The story of the Eritrean patriot Zar'
āy Daras. Partly in dramatic form.
Amharic text. 1949 A.M., 1957 A.D.]

160275

1602775
AND AFRICAN STUDIES

ታሪክ ፡ በቲያትረ ...

# ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

ተጻፈ ፡ ከአንተነህ ፡ ዓለሙ ፡

ዘብሔረ ፡ ጐጃም ፡

ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወፍኖተ ፡ ሰላም ።


አዲስ ፡ አበባ ፤ ግንቦት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤ ቍ 1607

SCHOOL OF ORIENTAL & AFRICAN STUDIES
LONDON

27.8.62

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ወይም ፡ ማራባት ፡ ክልክል ፡ ነው ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

የኢትዮጵያ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህን ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመውን ፡ መጽሐፍ ፡ በአነስተኛዋ ፡ ዕውቀቴ ፡ በጀግናውና ፡ በስመ ፡ ጥሩው ፡ ወንድማችን ፡ በዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ስም ፡ በጽሑፍ ፡ አዘጋጅቼ ፡ መጪው ፡ ትውልድ ፡ አስፋፍቶ ፡ ይሠራበታል ፡ በማለት ፡ አስቤ ፡ ያዘጋጀሁትን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ከገናናው ፡ ዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ሆኜ ፡ ይቀበሉኝ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ጃንሆይ ።

ምንም ፡ የጀግናው ፡ ወንድሜን ፡ ሙሉ ፡ ታሪኩን ፡ ባላገኘውም ፡ እንኳ ፡ ለጊዜው ፡ የተገኘውን ፡ ለቲያትር ፡ እንዲመች ፡ በቲያትር ፡ መልክ ፡ ለውጨዋለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነትና ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በሰው ፡ አደባባይ ፡ የሞተለትንና ፡ የወደቀለትን ፡ አሸናፊውን ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ በጥንት ፡ ክብሩ ፡ ላይ ፡ መመለሱን ፡ ምነው ፡ ዛሬ ፡ በሕይወት ፡ ሆኖ ፡ በየው ፡ በማለት ፡ ኅሊናዬን ፡ ሐዘን ፡ ይነካውና ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሳመዛዝነው ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ካገሪቱ ፡ የተወሰዱትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያዎችና ፡ ሐውልቶች ፡ በሙሉ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ትጋት ፡ ተመልሰውና ፡ የጀግናውም ፡ የወንድማችን ፡ ዐፅም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ በክብር ፡ መጥቶ ፡ ለሞተላት ፡ ለውድ ፡ ሀገሩ ፡ ዐፈር ፡ በቅቶ ፡ ሳይ ፡ በሕይወት ፡ እንዳለ ፡ ቈጥሬው ፡ ሐዘኔ ፡ ወደ ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ይለወጣል ።

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ምንም ፡ ያገራችን ፡ የጀግንነት ፡ ታሪክና ፡ ደግሞም ፡ ብዙ ፡ ባለታሪኮች ፡ ቢኖሩም ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ትጋት ፡ በዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ተስፋፍተው ፡ የሚገኙት ፡ የታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በየድርሰቶቻቸው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ ስማቸውንና ፡ ሥራቸውን ፡ እያጋነኑ ፡ ሲጽፉ ፡ ይታያሉ ። እንሆ ፡ እኔም ፡ ቅን ፡ ታዛዥዎ ፡ ሰው ፡ ሰውን ፡ ያያል ፤ ራሱን ፡ ለማየት ፡ ግን ፡ መስተዋት ፡ ያስፈልገዋል ፡ በማለት ፥ ማንበብ ፡ ብቻ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ስላልታየኝ ፡ የችሎታዬን ፡ ያኽል ፡ ይችን ፡ አነስተኛ ፡ ድርሰቴን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ በኢትዮጵያዊነቴ ፡ እየኰራሁ ፡ ነው ።



አነስተኛው ፡ ድኻዎ ፡
አንተነህ ፡ ዓለሙ ።

ኢ ትዮጵያ ፡ እናት ፡ ወልዳ ፡ ተሞሽራ ።
ት ውልድን ፡ የአኰራች ፡ ለዓለም ፡ ስታበራ ፡
ዮ ሐንስ ፡ ዘንድሮ ፡ የአራስ ፡ ጥሪዋን ፡
ጵ ራቅሊጦስ ፡ በነግህ ፡ ገለጸላት ፡ ቃሉን ።
ያ ን ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ተራምደነዋል ፥
ን ዋሪ ፡ ሥራችንን ፡ በሥራ ፡ እናውል ፤

ሊ ከበር ፡ ይገባል ፡ የነጻነት ፡ በዓል ፡
ገ ናናው ፡ ተፈሪ ፡ የመሠረተው ፡ ውል ፡
ዛ ሬም ፡ ጠብቆ ፡ ታይቷል ፡ እንሆ ፡ በድል ።

ፋ ስ ፡ መጥረቢያ ፡ ስለት ፡ ከፋሺስት ፡ ታዞ ፡
ሺ ብርና ፡ ዕልቂት ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ተመዞ ፤
ሺ ብሩም ፡ ረጋ ፡ ዕድሜ ፡ ለጃንሆይ ፡
ት ዳሩም ፡ አማረ ፡ በምድር ፡ በሰማይ ።

ተ መስገን ፡ እንበለው ፡ ፈጣሪያችንን ፡
መ ርጦ ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፡ አባ ፡ ጠቅልን ፤
ኜ ንቴ ፡ ብሎ ፡ ሄደ ፡ ፋሺስት ፡ በሙሉ ፡

ጀ አሎ ፡ መገን ፡ ሲሉ ፡ አርበኞች ፡ በሙሉ ፡
ግ ፈኞች ፡ ወደቁ ፡ ተገፊዎች ፡ አሉ ።
ና የአገሬ ፡ ወጣት ፡ አንብብ ፡ ታሪክህን ፡

ስ ለኢትዮጵያ ፡ የተጻፉትን ፡
ው በቷንም ፡ ሆነ ፡ ሙሉ ፡ ታሪኳን ።
ቢ ነበብ ፡ አያልቅም ፡ የኛ ፡ ጀግንነት ፡
ፊ ላስፋዎች ፡ አሉ ፡ ስለኛ ፡ ትምህርት ፡
ለ ውጭ ፡ እንበቃለን ፡ ለበጎ ፡ ትምክሕት ፡
ግ ሩም ፡ ነው ፡ ታሪኳ ፡ የኢትዮጵያ ፤

ተ ጽፎም ፡ አያልቅ ፡ የተፈሪ ፡ ሞያ ።
ፊ ራጆች ፡ ፈረዱ ፡ በውነት ፡ አስበው ፡
ሪ ኰርዱ ፡ ታየ ፡ በመጀመሪያው ፡
ተ ረከበች ፡ በሯን ፡ ያሰበችውን ።
ገ ረመው ፡ በሙሉ ፡ ለውጭው ፡ እንግዳ ፡
ኛ ንቴ ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ ሲያስወጣው ፡ ከሜዳ ።

## መቅድም ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ብዬ ፡ የሰየምኩበት ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ጀግና ፡ የጀግንነቱን ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ አደራ ፡ የሚጣለው ፡ በታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ በማስታወስ ፡ መጪው ፡ ትውልድ ፡ አስፋፍቶ ፡ እንዲሠራበት ፡ በማለት ፡ ከሙሉ ፡ በክፍሉ ፡ የጀግናውን ፡ ታሪክ ፡ በመጥቀስ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ብዬ ፡ ሰይሜዋለሁ ።

## አንባቢ ፡ ሆይ ።

ስመ ፡ ጥሩው ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ሰይፍ ፡ መዞ ፡ ስለ ፡ ክብሩ ፡ መጋደሉ ፡ የሚያኰራው ፡ ማንን ፡ ይመስልሃል ፤ በመላው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ አይደለምን ? ጀግናውም ፡ ሕይወቱን ፡ በነጻነቱ ፡ የለወጠው ፡ የአገሩን ፡ ክብር ፡ አሳውቆ ፡ በታሪክ ፡ ላይ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ለመሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በከንቱ ፡ አለመሆኑን ፡ ከተከበሩ ፡ አንባቢዎች ፡ እንደማይሰወር ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።

ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ መጽሐፍ ፡ ለምትመለከቱ ፡ ለክቡራን ፡ አንባቢዎች ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ የማሳስባችሁ ፡ መጀመሪያ ፡ ከመንቀፍ ፡ ከመነሻው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ተመልክታችሁ ፡ ውጤቱን ፡ ማግኘት ፡ የአስተዋዮች ፡ ፈንታ ፡ መሆኑን ፡ እያሳሰብኩ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ሲጀመር ፡ ያለአንድ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ያለአንድ ፡ መነሻ ፡ እንደማይጀመር ፡ አንባቢ ፡ አይስተውም ።

ይህንንም ፡ ድርሰት ፡ ለመጽሐፍ ፡ ያሳሰበኝ ፡ በየጓሊናችን ፡ ላይ ፡ ተቀርጾ ፡ የሚኖረው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ከባድ ፡ አደራ ፡ ነው ።

«እንደምታውቁት ፡ ሁሉ ፡ ከሌላው ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ የኛ ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የዘገየውና ፡ በሰፊው ፡ ሊራባ ፡ ያልቻለው ፡ የጸሓፊዎች ፡ ቍጥር ፡ በማነሱና ፡ የደራስያን ፡ ሥራ ፡ በትክክል ፡ ባለመራመዱ ፡ ነው ።

የጽሕፈት ፡ ሙያ ፡ በቀላሉ ፡ የሚገመት ፡ አይደለም ፤ መላው ፡ ዓለም ፡ በጽሑፍ ፡ ረገድ ፡ ከኛ ፡ በጣም ፡ ርቆ ፡ ሄዷል ። እናንተም ፡ ጥቂት ፡ ለማንበብና ፡ ለመጻፍ ፡ የቻላችሁት ፡ ብዙዎች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ደራስያን ፡ ከጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ በቀሠማችሁትና ፡ ባጠናችሁት ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ደሙንና ፡ ሕይወቱን ፡ ለሀገሩና ፡ ለወገኑ ፡ ጠቃሚ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ መሥዋዕት ፡ በማድረግ ፡ ያሰበውን ፡ ተግባር ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ለማድረስ ፡ ቍርጠኛ ፡ የሆነ ፡ ነው ።

የናንተ ፡ ሙያ ፡ የሚታወቀው ፡ አሁን ፡ አይደለም ፤ ጊዜና ፡ ትውልድ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሥራችሁና ፡ ስማችሁ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባዲስ ፡ መልክ ፡ ቀርቦ ፡ ታሪክ ፡ ሲያስታውሰው ፡ ነው ።

የጽሑፍ ፡ ፍሬዋ ፡ ካፈራ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የናንተም ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የሚታወቀው ፡ ካለፋችሁ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ እናንተ ፡ የጻፋችሁትን ፡ ማስታወሻ ፡ ይዞ ፡ የሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ሲጠቀምበት ፡ ነው ።

ሰው ፡ የችሎታውን ፡ ያኽል ፡ ሲጽፍ ፡ ላገሩና ፡ ለወገኑ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፡ ይቈጠርለታል ፤ ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ የሚቈጠርላት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ ጥንታዊት ፡ አገር ፡ ስትሆን ፡ በታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ እንደርምጃዋ ፡ መጠን ፡ የተሞላ ፡ አይደለም ።

## መቅድም ።

አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ሄደን ፡ በጐበኘንበት ፡ ጊዜ ፡ በመጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ የተመለከትናቸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛሉ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመላው ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገኝ ፡ ያወጣንለትን ፡ ዐዋጅ ፡ ሰምታችሁታል ። ይህም ፡ ዐዋጅ ፡ ሁሉንም ፡ የጽሕፈትና ፡ የማንበብ ፡ ችሎታ ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚረዳው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እናንተም ፡ ማንበብን ፡ መሠረት ፡ አድርጋችሁ ፡ እውነተኛውን ፡ ለትውልድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ታሪክ ፡ መጻፍ ፡ አስከትሉ ።


አሁን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ስንቀበላችሁ ፡ የምንነግራችሁ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሠራችሁት ፡ የሚያስመሰግን ፡ መሆኑን ፡ ልንገልጽላችሁና ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ በዚሁ ፡ እንድትጠነክሩበት ፡ ልናበረታታችሁ ፡ ነው» ።

ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡

ኅዳር ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ አደራ ፡ በማስታወስ ፡ ይችን ፡ አነስተኛ ፡ የሆነችውን ፡ ድርሰቴን ፡ ለመጻፍ ፡ ኅሊናዬ ፡ ቀሰቀሰኝ ። ስለዚህ ፡ የማይሳሳት ፡ የማይሠራ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የተከበራችሁ ፡ አንባቢዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሳስቼ ፡ ብገኝ ፡ በጐደለ ፡ እየሞላችሁ ፡ በቀና ፡ ኅሊና ፡ እንድትመለከቱልኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

አንተነህ ፡ ዓለሙ ።



የ፳፭ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ያበረከቱ ፡ ደራስያን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተ ጠቀሰውን ፡ ንጉሣዊ ፡ መፈ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ በዓሉ ፡ የክብር ፡ ሜዳይ ፡ ተሸልመው ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲወጡ ፡ ያሳያል ።

## ታሪክ ፡ በቲያትር ፡ መልክ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የአስመራ ፡ አገረ ፡ ገዥ ።


ኢትዮጵያን ፡ ወረን ፡ ድል ፡ ያደረግንበት ፡
በዓሉ ፡ ተቃረበ ፥ መከበር ፡ አለበት ።
የኤርትራን ፡ ዜጎች ፡ ለፖለቲካችን ፡
ታላላቅ ፡ ሰው ፡ መርጠን ፡ ሽማግሌዎችን ፡
ሮማ ፡ ላይ ፡ ወስደን ፡ ማስደሰት ፡ አለብን ።
ባላባቶችን ፡ ወስደን ፡ ሮማ ፡ ከተማ ፡
እስቲ ፡ እናዋርዳቸው ፡ ዓለም ፡ እንዲሰማ ።
እንዲያውም ፡ ኃይላቸው ፡ የነሱ ፡ ምልክት ፡
የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ብለው ፡ ሲመኩበት ፡
ኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ከነሱ ፡ ቀምቶት ፡
ወስዶ ፡ አስቀምጦታል ፡ ሮማ ፡ በጉልበት ።
እስቲ ፡ እናሳያቸው ፡ አገራችንን ፡
በጹፍም ፡ ባርነት ፡ እንዲገዙልን ።
መጥተው ፡ እንዲሰብኩ ፡ ወገኖቻቸውን ፡
ያስፈልጋል ፡ በግድ ፡ ለነሱ ፡ ማሳየት ፡
የኛን ፡ ክብር ፡ የኛን ፡ ኀይል ፡ የፋሺስትን ፡ ጉልበት ።
እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ይኸ ፡ ተሰምቶኛል ፡
እስቲ ፡ አንተም ፡ አማክረኝ ፡ ምክር ፡ ሰው ፡ ይጠቅማል ።

### ያገረ ፡ ገዡው ፡ አማካሪ ።

ይገርማል ፡ ይደንቃል ፡ የዛሬው ፡ አሳብ ፤
ከወዴት ፡ ይገኛል ፡ እንዲህ ፡ የሚያስብ ።
መልካም ፡ ነው ፡ አሳብህ ፡ በጣም ፡ ተስማምቶኛል ፤
ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ አሳብ ፡ ይገኛል ።



ድል ፡ አድራጊው ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ።



የ፳፻ ፡ ዓመት ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

ሰዎች ፡ አስመርጠን ፡ ሽማግሌዎች ፡
በዕድሜ ፡ የበሰሉ ፡ ባለታሪኮች ፡
በሰው ፡ ተፈልገው ፡ ከዚሁ ፡ ከተማ ፤
ይሂዱ ፡ በቶሎ ፡ ወሬ ፡ ሳይሰማ ፤
አስተርጓሚ ፡ መርጠህ ፡ ለኔ ፡ የሚስማማ ፡
ሳትውል ፡ ሳታድር ፡ ተነሥ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡
ብለህ ፡ እዘዝና ፡ አንዱን ፡ ወታደር ፡
እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ሸኛቸው ፡ በእግር ።

ሽማግሎች ፤ መልካም ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ እናከብረዋለን ፡
የበዓሉን ፡ ሁናቴ ፡ ምስጢሩን ፡ ካወቅን ፡
የዛሬው ፡ በዓልማ ፡ ለኛ ፡ ታሪክ ፡ ሆነን ።
እረ ፡ ለመሆኑ ፡ እዚያ ፡ አገር ፡ ስንሄድ ፡
ቋንቋችን ፡ ለአገሩ ፡ በጣም ፡ አይለመድ ፡
አንድ ፡ አስተርጓሚ ፡ እኮ ፡ ሊያስፈልግ ፡ ነው ፡ በግድ ።

አገሪ ፡ ገዥው ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አማከርከኝ ፡ ደግሞ ፤
ያላስተርጓሚማ ፡ አይሆንም ፡ ፈጽሞ ።
አሁን ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ የምትሄዱበት ፡
የኛን ፡ ታሪክና ፡ የኛን ፡ ገናናነት ፡
እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ የናንተን ፡ ሞኝነት ፡
እንድትረዱት ፡ ነው ፡ ሁሉንም ፡ ባንድነት ።
ስለዚህ ፡ ሐሳብህ ፡ በጣም ፡ ተስማምቶኛል ፤
መልካም ፡ አስተርጓሚ ፡ ከወዴት ፡ ይገኛል ።

ሽማግሌው ፤ አስተርጓሚስ ፡ አለ ፡ ዐዋቂ ፡ ወጣት ፡
በጣም ፡ የደረጀ ፡ በጥበብ ፡ በውቀት ፤
ስሙን ፡ እንኳ ፡ ወንድሜ ፡ ማን ፡ ነበር ፡ ያሉት ።
ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ነው ፡ የወጣቱ ፡ ስም ፤
እስቲ ፡ ይጠራና ፡ ጠይቀው ፡ አንተም ።

ተጠርቶ ፡ ይምጣና ፡ እዚህ ፡ አንተ ፡ ፊት ፡
ይሂድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስምምነት ፤
ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ የኔ ፡ ሐሳብ ፡ ይጠቅማል ፤
እዚሁ ፡ ተጠርቶ ፡ ቢጠየቅ ፡ ይሻላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ይጠራና ፡ ወደ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ ትእዛዝ ፡ ካገረ ፡ ገዥው ፡ ይቀበላል ።

አገረ ፡ ገዥው ፤ ስማህ ፡ አንተ ፡ ወታደር ፡ ስትሮጥ ፡ ሂድና ፡
ጄኔራሉ ፡ ጠሩህ ፡ እንሂድ ፡ በልና ፡
ዘርዓይን ፡ ይዘኸው ፡ በፍጥነት ፡ ቶሎ ፡ና ።

መልክተኛው ።

እሺ ፡ ጄኔራሌ ፡ መልክት ፡ በማክበር ፡
ትእዛዝ ፡ ፈጻሚና ፡ ታዛዥ ፡ ነው ፡ ወታደር ።

ወታደሩም ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጥና ፡ ወደ ፡ ተላከበት ፡ ወደ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ይሄዳል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ወታደሩ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ቤት ፡ ይደርሳል ፤ ዘርዓይ ፡ ወዳለበት ፡ ክፍል ፡ ይገባና ፡ ሰላምታ ፡ ይሰጣል ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ስማህ ፡ ወይ ፡ ወዳጄ ፡ ከወዴት ፡ መጥተሃል ፥
ለሁሉ ፡ አለሁ ፡ ብለህ ፡ እዚህ ፡ ተልከሃል ፤
ደግሞ ፡ ዛሬ ፡ እስቲ ፡ ምን ፡ ይዘህ ፡ መጥተሃል ።

መልክተኛው ።

ለሁሉ ፡ አለሁ ፡ ማለት ፡ በጣሙን ፡ መልካም ፡ ነው ፤
የማመጣው ፡ ሁሉ ፡ ለርስዎ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

እጅግ ፡ ያስደስታል ፡ ዛሬስ ፡ ብነግርዎ ፡
አይነግሩብኝ ፡ እንደሁ ፡ ምስጢር ፡ ላካፍልዎ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

ለማንም ፡ አልነግር ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ በጭራሽ ፤
የተላከውን ፡ መልክት ፡ ምንም ፡ ሳታበላሽ ፥
ምስጢሩን ፡ አካፍላኝ ፡ ሁሉን ፡ በዝርዝር ፡
ፍሬ ፡ ያለው ፡ እንደሆን ፡ የሚያስገኝ ፡ ነው ፡ ክብር ።
ንገረኝ ፡ ዘርዝረህ ፡ በዚህ ፡ አታስብ ፡
በዚህ ፡ አያገኝህም ፡ በፍጹም ፡ ሰበብ ።

መልክተኛው ።

እንዲህ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ የተላኩት ፡ መልክት ፡
ያገሩን ፡ ባላባት ፡ ሁሉንም ፡ ባንድነት ፡
ሮማ ፡ ይሂዱ ፡ ብለው ፡ መከሩበት ።
አብሯቸው ፡ የሚሄድ ፡ አስተርጓሚ ፡ አጥተው ፡
አብረው ፡ እንዲሄዱ ፡ በርስዎ ፡ ተስማምተው ፡
ሊሄዱ ፡ ነውና ፡ እርስዎም ፡ አብረው ፥
ለሞትም ፡ እንደሆን ፡ ወይም ፡ ለእስራት ፡
እኔ ፡ ግን ፡ አላውቅም ፡ እርስዎ ፡ አስቡበት ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

የማስተረጕመው ፡ እኔ ፡ ሮማ ፡ ሄጄ ፡
ምኑን ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ሰማህ ፡ ወይ ፡ ወዳጄ ።
እነሱ ፡ እንደሆን ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ የገቡት ፡
በትልቅ ፡ እብሪት ፡ ነው ፡ በጣሙን ፡ በትዕቢት ።
የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ አይደመሰስም ፡
ደግሞም ፡ መታሰቢያ ፡ እንደዚህ ፡ አይፈርስም ፡

የተባለውን ፡ ቃል ፡ ከታላቁ ፡ መሪ ፡
ከኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡
እነሱ ፡ ሆነዋል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሻሪ ።
በነጋ ፡ በነጋ ፡ እኔን ፡ እያስጠሩ ፡
የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ አንተ ፡ ሻር ፡ እያሉ ፡
እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገር ፡ አስተርጕም ፡ ይላሉ ።
እንደ ፡ ገና ፡ ወስደው ፡ እኔን ፡ እባዕድ ፡ አገር ፡
ከፉውን ፡ ደግ ፡ አርገህ ፡ ሊሉኝ ፡ ነው ፡ ተናገር ፡
የአገሬን ፡ ታሪክ ፡ ሁሉንም ፡ በዝርዝር ፡
የኢትዮጵያን ፡ መወረር ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ላከብር ።
መሄዴስ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እኔም ፡ እሄዳለሁ ፤
የምሠራውንም ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ዐውቃለሁ ።
አንተም ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡
የተመከረውን ፡ ስለ ፡ ገለጽክልኝ ።
በል ፡ ሂድ ፡ እመጣለሁ ፡ ልብሴን ፡ ለባብሼ ፡
አልቀርም ፡ እመጣለሁ ፡ ቍርስ ፡ መሳይ ፡ ቀምሼ ።

መልክተኛው ፡ እጅ ፡ ይነሣና ፡ ይሄዳል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

መልክተኛው ፡ የመልክቱን ፡ መልስ ፡ ለማድረስ ፡ ወዳ አገረ ፡ ገዥው ፡ ይገባል ።

አገረ ፡ ገዥው ፤ መጣህ ፡ አንተ ፡ ወታደር ፡ መልክቱን ፡ አድርሰህ ፡
አንተ ፡ እኮ ፡ ለኛ ፡ ሕዝብ ፡ በጣሙን ፡ ታማኝ ፡ ነህ ፡
በል ፡ እንጂ ፡ እባክህን ፡ አገኘኸው ፡ ወይ ፡
ዐዋቂ ፡ ያሉትን ፡ በጣም ፡ አስተዋይ ።

መልክተኛው ፤ አወን ፡ አድርሻለሁ ፡ የኔ ፡ ጀኔራል ፥
መልክቱን ፡ ነግሬው ፡ አሁን ፡ ይመጣል ፤
በጣም ፡ ተደስቶ ፡ እሺ ፡ ብሎኛል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ይመጣል ፤ አገረ ፡ ገዥው ፡ ወዳለበት ፡ ይገባል ፡፡

አገረ ፡ ገዥው ፤ መጣ ፡ እንዴ ፡ አስተርጓሚው ፡ ጥሪውን ፡ አክብሮ ፡
እውነትም ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ባለአእምሮ ፡፡
አሁንም ፡ አስገቡት ፡ እስቲ ፡ ልየው ፡ መልኩን ፡
ከቤቱ ፡ መንግሥቱ ፡ ከዋናው ፡ ሳሎን ፤

አሽከር ፡ ይጠራውና ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ወዳሉበት ፡ ሳሎን ፡ ይዞት ፡ ይገባል ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደንቡ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እጅ ፡ መዘርጋት ፡ ነበር ፤ እሱ ፡ ግን ፡ እንዳገሩ ፡ ልማድ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ አለ ፡፡

አገረ ፡ ገዥው ፤ አንተ ፡ ነህ ፡ ለካ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ማለት ፡
ዝናህ ፡ የከበደኝ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ አንዱበት ፡፡
ትልቅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሲያሞጋግሱህ ፡
ለካ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የአንተ ፡ ዕውቀትህ ፤
በዓለም ፡ ለታወቀው ፡ ለፋሺሽት ፡ መንግሥት ፡
ለምን ፡ ነው ፡ የኰራህ ፡ ሰላምታ ፡ ለመስጠት ፡፡

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ በኛ ፡ አገር ፡ ክልክል ፡ ነው ፡ እጅ ፡ መዘርጋት ፤
ልብሴ ፡ አይፈቅድልኝም ፡ ሰላም ፡ ለማለት ፡፡
ሰላምታ ፡ የሚሰጥ ፡ ወታደር ፡ ብቻ ፡ ነው ፥
እረ ፡ ለአንድ ፡ ሲቪል ፡ ሰላምታ ፡ ምኑ ፡ ነው ፤
እጅ ፡ መዘርጋትስ ፡ ምስጢሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡፡
እኔስ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አክብሬ ፡ ነበረ ፡
እጅ ፡ የነሣሁዎት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ፡፡

አገረ ፡ ገዥው ፤ እንዴት ፡ ያለው ፡ እሳት ፡ የማይቻለው ፡ ነው ፥
አንድ ፡ ሲናገሩት ፡ መልሱ ፡ ሦስት ፡ አራት ፡ ነው ፤
አላናግር ፡ አለኝ ፡ እኔ ፡ እንዳልጠይቀው ፡፡

የሐበሾችን ፡ ሕግ ፡ ወደዚያ ፡ ጣልና ፡
እኔ ፡ የምልህን ፡ ሰላምታ ፡ ስጥና ፡
የምታደርገውን ፡ እኔ ፡ ስነግረህ ፡
በጸጥታ ፡ አዳምጠኝ ፡ ትዕቢት ፡ ይቅርብህ ።
ስለሚደረገው ፡ ጕዞና ፡ ታሪክ ፡
እባክህ ፡ እሺ ፡ በል ፡ ሰውን ፡ አታውክ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ እሽ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ከጠቀመዎማ ፡
ይኸው ፡ ዘረጋሁት ፡ እጄን ፡ እንደማማ ።

አገረ ፡ ገኘው ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አጭር ፡ ነገር ፡ ሳለ ፡
ልብህ ፡ ባጕል ፡ ትቢት ፡ እየተከፈለ ፡
አሁንም ፡ አትርሱት ፡ ይህንን ፡ ታሪክ ፡
መስገድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ለፈጠረ ፡ አምላክ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ባገራችን ፡ ልማድ ፡ እርስዎን ፡ ሳከብር ፡
ለኔ ፡ የሚገባኝ ፡ ሽልማት ፡ ነበር ፤
ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በርስዎ ፡ ባሰና ።
ይቈጡኝ ፡ ዠመረ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ገና ።

ጀኔራሉ ፡ በክርክሩ ፡ በጣም ፡ ተደንቆ ፡ ከመደነቁም ፡ የተነሣ ፡ አንገቱን ፡ እየነቀነቀ ፡ ጥቂት ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ የሚከተለውን ፡ ይናገራል ።

አገረ ፡ ንኘው ፤ አሁን ፡ እዚህ ፡ ስፍራ ፡ አንተን ፡ ያስጠራሁህ ፡
እንድትሄድ ፡ ነው ፡ ሮማ ፡ ተልከህ ።
እንድታስተረጕም ፡ ተመርጠሃልና ፡
ከሽማግሎች ፡ ጋር ፡ እንድትሄድ ፡ ያውና ።
እኔ ፡ በበኩሌ ፡ አደራ ፡ የምልህ ፡
አለ ፡ መታሰቢያ ፡ ላንተ ፡ የምሰጥህ ፤
ወስደህ ፡ እንድትሰጠው ፡ መታሰቢያውን ፡
ሌሎችን ፡ አላምንም ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ይሁን ።

ይህን ፡ ጣፋ ፡ ጋሻና ፡ ባለሙጣ ፡ ሰይፍ ፡
ዳግም ፡ አንፋሮና ፡ ጐፈር ፡ ጨምረህ ፡
እንድትሰጥልኝ ፡ ሮማ ፡ ወስደህ ፡
እምነቴን ፡ በሙሉ ፡ ባንተ ፡ ጥያለሁና ፡
እንድትሰጥልኝ ፡ አደራ ፡ ያውና ።

ዘርዓይ ፡ ደረስም ፡ ዕቃውን ፡ ተቀበለና ፡ የሚከተለውን ፡ ተናገረ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ይህ ፡ የሚላከው ፡ የሀገር ፡ ላንቲካ ፡
ለሮማውያኖች ፡ ዋና ፡ ፖለቲካ ፡
እኔ ፡ እዚያ ፡ አገር ፡ ስሄድ ፡ እርስዎ ፡ ሲልኩኝ ፡
ታሪኩን ፡ በሙሉ ፡ ማስረዳት ፡ አለብኝ ፤
ይልቁንም ፡ ደግሞ ፥ ይህን ፡ ማስታወሻ ፡
ከነታሪኩ ፡ ነው ፡ ማስረከብ ፡ የሚያሻ ።
የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፡
ብዬ ፡ ሳስረዳቸው ፡ ልብሱ ፡ እንደ ፡ ከበረ ፤
ጀግኖች ፡ አባቶቼ ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡
በየጐራውና ፡ በየጦሩ ፡ ስፍራ ፡
ሁሉን ፡ በማስረዳት ፡ ልብሱን ፡ እንደ ፡ ለበስሁ ፡
ለሮማውያኖች ፡ አሳያቸዋለሁ ።

ካለ ፡ በኋላ ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ በጣም ፡ ተገርሞ ፡ ሐሳብህ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ በሮማውያን ፡ ኃይልና ፡ ጭካኔ ፡ ተዋርደው ፡ ድል ፡ ከተመቱ ፡ በኋላ ፡ ማስታወሻቸውና ፡ ታሪካቸው ፡ በኛ ፡ በሮማውያኖች ፡ እጅ ፡ ተጥሎ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማቸውም ፡ በኛ ፡ ኃይል ፡ ከበታው ፡ ጠፍቶ ፡ የእንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ የጀግኖች ፡ አገር ፡ ከ3000 ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ ዝምራ ፡ ነጻነቷን ፡ ጠብቃበት ፡ የምትኖረውን ፡ ዋናውን ፡ የጦር ፡ ኃይሏን ፡ ሰይፍ ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ እንዲሁም ፡



ዘርዓይ፡ ደረስ።

የጦር፡ ልብስ፡ ጐፈር፡ ኢትዮጵያን፡ ለመውረር፡ በመጣን
በት፡ ጊዜ፡ ባድዋ፡ ጦር፡ ሜዳ፡ በኛው፡ አንገት፡ የተጫ
ወተውን፡ ሰይፍ፡ ለጓደኛዬ፡ ስልክለት፡ ለኔ፡ (በጣም)፡ ኵ
ራት፡ ይሰማኛል፡ በውነቱ፡ እኔም፡ ራሴ፡ ባይኔ፡ ታሪኩ
ን፡ ማየት፡ ያስፈልገኛል፡ አለና፡ ልብሱን፡ አልብሶ፡ ያገ
ሩን፡ ታሪክ፡ እንዲያስረዳው፡ አስገደደው። ዘርዓይ፡ ደረ
ስም፡ የተመኘነው፡ ስለ፡ ተፈጸመለት፡ ያገሩን፡ ጋሻና፡ ጦር፡
ከነሰይፉ፡ ደንበኛ፡ የኢትዮጵያን፡ የጦር፡ ልብሱን፡ ለብሶ፡

እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንቈራጠጠ ፡ ያስረዳው ፡ ዠመር ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ምነው ፡ ትከሻዬን ፡ በጣሙን ፡ ሞቀኝ ፡
ነጻነት ፡ ኵራቴን ፡ ደረብኩ ፡ መሰለኝ ፤
አንቺ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ አቤት ፡ ስታምሪብኝ ፡
የአገሬ ፡ ምልክት ፡ አንች ፡ እየመሰልሽኝ ፡
ባለ ፡ ታሪኳ ፡ ሰይፍ ፡ ቍጭ ፡ በይ ፡ በጐኔ ፡
ያስታወስኩሽ ፡ እንደሆን ፡ ታፈሊያለሽ ፡ ወኔ ።
ወይኔ ፡ አንበሳው ፡ እንደምን ፡ ተደፈርሁ ፤
እጠላቴ ፡ አጠገብ ፡ ቆሜ ፡ እሚወቃለሁ ።
ኢትዮጵያ ፡ አገሬ ፡ ዕድሏ ፡ ተሰብሮ ፡
እንዲህ ፡ ሊቀር ፡ ነው ፡ ወይ ፡ በጠላት ፡ ተወሮ ፤
አለመተባበር ፡ የሚያመጣው ፡ ውርደት ፡
ታሪክ ፡ ተሸክሜ ፡ ልሄድ ፡ ነው ፡ በመልክት ፡
ከአገሬ ፡ ወጥቼ ፡ እሮማ ፡ በስደት ፤
መልክቱ ፡ እንኳ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነበረ ።
ጓደኛ ፡ ቢኖረኝ ፡ ልቡ ፡ የመረረ ፡
ሥራ ፡ አይጠፋም ፡ ነበር ፡ ሰው ፡ ከተባበረ ።
ሮማውያኖች ፡ ከጥንት ፡ ዠምረው ፡
በፍጥረት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ቀለዱ ፡ ነው ።
ዛሬም ፡ ይኸውና ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ገና ፡
ታሪክ ፡ አሸከመው ፡ በውርደት ፡ ጐዳና ፤
እኔ ፡ ግን ፡ የአገሬን ፡ ታሪክ ፡ አጥንቼዋለሁ ፥
ታሪክ ፡ ለሚያጠና ፡ አስተምራለሁ ፤
ማስታወስ ፡ ይገባል ፡ የዐድዋን ፡ ታሪክ ፡
የተፈጸመውን ፡ ባዬ ፡ ምኒልክ ።
ታሪኳ ፡ ሲነገር ፡ የኢትዮጵያ ፡
በሰይፍ ፡ ገራፊ ፡ በታሪክ ፡ ገባያ ፤

በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ታሪክ ፡ የሰራ ፡ ሰው ፡
የማይሞት ፡ ስምና ፡ ክብር ፡ ነው ፡ የሚወርሰው ፤
ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ እኔ ፡ የማስበው ፡
በታሪክ ፡ ገባያ ፡ ገሎ ፡ መሞትን ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ ያገሬ ፡ ጀግኖች ፡ ሁሉም ፡ ባንድነት ፡ ለክብራቸውና ፡ ለነጻነታቸው ፡ ጊዜያቸውን ፡ ሁሉ ፡ በክብር ፡ አሳለፉት ፡ ይልና ፡ ንግግሩን ፡ ሲያቆም ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ከመገረሙና ፡ ከመደነቁ ፡ የተነሣ ፡ በጣም ፡ ሥቆ ፡ የሚከተለውን ፡ ይናገራል ።

አገረ ፡ ገዥው ፤ ሰማህ ፡ ወይ ፡ ዘርዓይ ፡ አሁን ፡ ስታስረዳኝ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አድርገህ ፡ በጣም ፡ አስደሰትኸኝ ።
ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እኔ ፡ እምለምንህ ፡
ልብሱን ፡ አውልቅና ፡ በክብር ፡ አስቀምጠህ ፡
ሌላ ፡ ልብስ ፡ ለውጥ ፡ ለጕዞህ ፡ ተስማሚ ፡
እዚያው ፡ አገር ፡ ስትሄድ ፡ ስትሆን ፡ አስተርጓሚ ፡
ይህን ፡ ልብስ ፡ ለብሰህ ፡ ሮማ ፡ ከተማ ፡
የኛ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ እናንተን ፡ ሲያዩማ ፡
ለፖለቲካችን ፡ በጣሙን ፡ ተስማማ ።
ሽማግሌዎችን ፡ እንዳይከፉቸው ፡
የኛን ፡ ኃይለኛነት ፡ በጣም ፡ አስረዳቸው ።
ደግሞ ፡ ስትመለስ ፡ ይህንን ፡ ፈጽመህ ፡
ታላቅ ፡ ሽልማት ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የምሸልምህ ።

ይልና ፡ በጣም ፡ አክብሮና ፡ አመስግኖ ፡ አሰናበተው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ሰላምታ ፡ ከተሰጣጡ ፡ በኋላ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ አንዱ ፡ የሚከተለውን ፡ ይጠይቀዋል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

ምክንያቱ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ የተጠራንበት ፤
ልትሄዱ ፡ ነው ፡ አሉን ፡ እሮማ ፡ በመልክት ።
መልክቱ ፡ ምንድነው ፡ እባክህ ፡ ንገረን ፤
በተቻለህ ፡ መጠን ፡ በአሳብህ ፡ እርዳን ፡
ወደነሱ ፡ ሆነህ ፡ እኛን ፡ አትደብቀን ።



ይህ ፡ ሥዕል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባላባቶች ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ የሚሄዱበትን ፡ ጉዳይ ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ ሲመካከሩና ፡ ሲወያዩ ፡ ያሳያል ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ የምንሄድበት ፡ እሮማ ፡ ተልከን ፡
የአገራችንን ፡ ሰይፍ ፡ ተሸክመን ፡
ሮማ ፡ ውስጥ ፡ ሄደን ፡ በሰፊው ፡ ከተማ ፡
በሰልፍ ፡ መካከል ፡ ታሪክ ፡ ልንሰማ ፡

እናንተንም ፡ ጠርተው ፡ እዚያው ፡ መውሰዳቸው ፡
እኔንም ፡ እንዲሁ ፡ አስተርጓሚ ፡ አድርገው ፡
የኛን ፡ ታሪክ ፡ ከናንት ፡ እየጠቀሁ ፡ እኔ ፡
ለአገሬ ፡ ጠላቶች ፡ ለኒያ ፡ ላረመኔ ፡
እንዳስረዳቸው ፡ ነው ፡ የተመረጥኩ ፡ እኔ ።

ከሽማግሎቹ ፡ ፩ዱ ፤ ይህማ ፡ ከሆነ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡
በክብር ፡ ስንላክ ፡ ከዚህ ፡ ስንሳፈር ፡
በነሱ ፡ ኪሳራ ፡ ሳንከፍል ፡ አንድ ፡ ብር ፡
ከአስመራ ፡ ተነሥተን ፡ ሮም ፡ ስንሻገር ፡
እኔ ፡ በበኩሌ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ክብር ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ይገርማል ፡ ይደንቃል ፡ የኛ ፡ ከብትነት ፡
እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ላም ፡ መነዳት ።
እሱ ፡ በበኩሉ ፡ ክብር ፡ አገኘሁ ፡ ብሎ ፡
የአገሩን ፡ ታሪክ ፡ በመርዝ ፡ ጠቅሎ ፡
ሮማ ፡ ሂድ ፡ ሲሉት ፡ ግፍን ፡ ተከትሎ ፡
ልቡ ፡ ይደሰታል ፡ ክብር ፡ አገኘሁ ፡ መስሎት ፡
የአገሩን ፡ ታሪክ ፡ በጭራሽ ፡ ረስቶት ፤
አይገርማችሁም ፡ ወይ ፡ እንደዚህ ፡ መሳሳት ።
በጣሙን ፡ ይደንቃል ፡ እናንተ ፡ አባቶቼ ፡
የአገራችን ፡ ነጻነት ፡ ተረስታ ፡ እስከ ፡ መቼ ፤
ጣፋጪ ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ ውዷ ፡ ነጻነት ፡
እንዴት ፡ እንሞታለን ፡ ታሪክ ፡ ሳናቄያት ።

፩ኛው ፡ ሽማግሌ ፤ ሰማህ ፡ ወይ ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ ይልቅስ ፡ ልምከርህ ፡
መሥራት ፡ በጊዜ ፡ ነው ፡ ሲባልም ፡ አልሰማህ ፤
እኛ ፡ በጊዜያችን ፡ በዐድዋ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡
የሮማን ፡ ወታደር ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ስንነዳ ፡

በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡
በዐድዋ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ታየ ፡ ጀግንነት ።
አሳይተናታል ፡ ለኢጣሊያን ፡ ወታደር ፡
ጦር ፡ ወርውሮ ፡ መግደል ፡ ሰይፍ ፡ መዞ ፡ መሰንዘር ።
ስለዚህ ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ እሙነት ፡ እልሃለሁ ፡
እንኳን ፡ ልዋጋና ፡ ስቃጣ ፡ እወድቃለሁ ።
እሮማ ፡ መድረሴን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፥
ወይም ፡ ከአንዱ ፡ ጕሬ ፡ ይጥሉኝ ፡ ይሆናል ፤
እሮማ ፡ ሂዱ ፡ ሲሉ ፡ እውነት ፡ መስሏችኋል ።

፩ኛ ፡ ሽማግሌ ፤ እኔ ፡ በበኩሌ ፡ የሚሰማኝ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
አሁን ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ ወንድሜ ፡ እንዳለው ፡
መሥራት ፡ በጊዜ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ተባለው ።
ባለጊዜዎቹ ፡ ይውጡ ፡ ይውረዱበት ፡
እግዜር ፡ ካረጋቸው ፡ ባለሙሉ ፡ሙብት ።
እሱ ፡ በቃ ፡ ሲለን ፡ ይህንን ፡ መከራ ፡
ቀን ፡ ይወጣልናል ፡ የነጻነት ፡ ጮራ ፤
አምላክ ፡ ቢቈጣን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ የሚሠራ ።
ስለዚህ ፡ እንጸልይ ፡ በበኩላችን ፡
እሱ ፡ በቃ ፡ ሲለን ፡ ይነሣል ፡ ኃይላችን ።

ይልና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ባንድነት ፡ የሚ
ከተለውን ፡ ይጸልያሉ ።

ኃይላችን ፡ ኃይላችን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
አውጣን ፡ ከባርነት ፡ ትልሃለች ፡ ነፍሴ ፡
ብለው ፡ ጕዟቸውን ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ለመሳፈር ፡ ይቀጥላሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

በተለየ ፡ ለነሱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ይሰጣቸውና ፡ እየተጨዋወቱ ፡ ሲጓዙ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ግን ፡ ከመርከቡ ፡ ውስጥ ፡ በመስኮት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ መርከቡ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ አገሩን ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ዠመር ።

ደኅና ፡ ሁኚ ፡ አገሬ ፡ ውቧ ፡ ኢትዮጵያ ፤
የሚፈጠርብሽ ፡ ጀግና ፡ ባለሙያ ።
አምላክ ፡ ተቀይሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተወራ ፡
ጀግኖቿ ፡ ሲዋጉ ፡ በሃይማኖት ፡ ካራ ፡
እኔ ፡ ዕድለ ፡ ቢሱ ፡ የጠላት ፡ ታማኝ ፡
ይግረመው ፡ እያለ ፡ ግፍ ፡ ሲቈጥርብኝ ፡
ለወገኑ ፡ እንድሰጥ ፡ መሣሪያ ፡ ሰጠኝ ፤
እንደ ፡ ኩብት ፡ ነድቶ ፡ አገሩ ፡ ላከኝ ።
ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሳመዛዝነው ፡
ሮማ ፡ መሄዴ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ፤
ሰይፍ ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ ይህን ፡ ተሸክሜ ፡ ስሄድ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡
ሥራ ፡ ብሠራበት ፡ እኔ ፡ ወጣቱማ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ክብሬ ፡ በተሰማ ።
በዚህ ፡ በሰጠኝ ፡ ሰይፍ ፡ እሮማ ፡ ገብቼ ፡
ዳግም ፡ በዚህ ፡ ጋሻ ፡ ጠላትን ፡ መክቼ ፡
ያገሬን ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ አሳያቸዋለሁ ፤
የጠላቴን ፡ አንገት ፡ በሰይፍ ፡ እቈርጣለሁ ።
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ሙሉ ፡ ሰውነቴ ፡
ሕይወቴ ፡ ላገሬ ፡ ሕይወቴ ፡ ለነጻነቴ ።

እያለ ፡ በሙሉ ፡ ቈራጥነት ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሲጓዝ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይጠሩትና ፡ ወዳሉበት ፡ ክፍል ፡ ይገባል ፤ ከውጭ ፡ ሲያ

ንጉራጉር ፡ ሰምቶ ፡ ኖሮ ፡ ከሽማግሌዎች ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

ሽማግሌው ፤ ሰማህ ፡ ወይ ፡ ዘርዓይ ፥ አንተ ፡ ስትመጣ ፡
ዐዋቂ ፡ ተብለህ ፡ ሰውን ፡ እንዳትቄጣ ፤
መርጠውህ ፡ ነበረ ፡ አስተዋይ ፡ ተብለህ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ አሳብ ፡ እረ ፡ ተው ፡ ይቅርብህ ።
አሁን ፡ ካለህበት ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ማዕርግ ፡
ይሻለኛል ፡ ብለህ ፡ እንደዚህ ፡ መባለግ ፡
ይቅርብህ ፡ እባክህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ብልግና ፡
ታሪክ ፡ እያጠናህ ፡ እንዲሁ ፡ በገና ፡
ታስጨርሰናለህ ፡ እኛን ፡ ሁላችንን ፡
ይልቅስ ፡ እንጓዝ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ዐርፈን ።
አንተ ፡ ልጅ ፡ እባክህ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ይቅርብህ ፤
እኔን ፡ እሺ ፡ በለኝ ፡ እረ ፡ በፈጠረህ ።
አንተ ፡ ይህን ፡ ሥርተህ ፡ ብቻህን ፡ አትሞትም ፤
ለኛ ፡ ሰበብ ፡ ሳትሆን ፡ ይልቅስ ፡ በሰላም ፡
የተላክህበትን ፡ በትክክል ፡ ሠርተህ ፡
ኢትዮጵያ ፡ ስትመጣ ፡ ትመሰገናለህ ፥
ሽልማትና ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ታገኛለህ ፤
ያን ፡ ጊዜ ፡ በጣሙን ፡ ለኛ ፡ ትተርፋለህ ፥
ልብ ፡ ያለህ ፡ እንደሆን ፡ ስማኝ ፡ ስመክርህ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ እኔ ፡ አልፈልገውም ፥
እኔ ፡ የምፈልገው ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ለወንድም ፤
ምያለሁ ፡ ለሞቴ ፡ ቈርጫለሁ ፡ በጣም ።
ይብላኝ ፡ ለድኾቹ ፡ ለናንተ ፡ በውነቱ ፡
መሞት ፡ አቅቷችሁ ፡ ለምትንገላቱ ።

እኔ ፡ ይልቅ ፡ አሳቤን ፡ በምክር ፡ ልርዳችሁ ፡
ለውዷ ፡ እናታችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገራችሁ ፡
እናንተ ፡ በትውልድ ፡ በድሜ ፡ በስላቻኋል ፥
ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ አጥንታችሁታል ፤
ሰው ፡ ላገሩ ፡ ሲሞት ፡ በጣም ፡ ያስደስታል ።
እኔ ፡ እናንተን ፡ ስመክር ፡ በጣም ፡ ቅር ፡ ይለኛል ፤
እኛው ፡ ካልተማከርን ፡ ማን ፡ ማንን ፡ ይመክራል ?
ስናመዛዝነው ፡ እንዴት ፡ ያስገርማል ፤
ነጻነት ፡ ተሸሮ ፡ ባርነት ፡ ተከብሯል ።
እናንተን ፡ መምከሬ ፡ እጅግ ፡ አጥፊ ፡ ነኝ ፤
እኔው ፡ ያሰብኩትን ፡ መሥራት ፡ አለብኝ ።
ቢሆንም ፡ አሳቤ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፡
ዛሬ ፡ ብንሠራ ፡ በመተባበር ፡
ለኛም ፡ ስማችን ፡ ነው ፡ ለኢትዮጵያም ፡ ክብር ።
በታሪክ ፡ ገበያ ፡ ትውልድን ፡ እናኰራ ፡
ጠላትን ፡ እንፍጀው ፡ በሃይማኖት ፡ ካራ ።
እንኳንስ ፡ እሮማ ፡ ጡብ ፡ አንሥተን ፡ ይቅርና ፡
የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ይፈራል ፡ በገና ።
እግዜር ፡ ከወደደን ፡ እኛን ፡ ተፈሪ ፡ አርጎ ፡
ሮማን ፡ እናርጋት ፡ የጀግንነት ፡ ሸንጎ ።
ይኸውም ፡ አሳቤ ፡ የተቃና ፡ እንዲሆን ፡
የነጻነት ፡ ጮራ ፡ የነጻነት ፡ ብርሃን ፡
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ርዳን ፡ ብለን ፡ እንለምን ።

፩ኛው ፡ ሽማግሌ ፤ እረ ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ እሻ ፡ ዝም ፡ በሉ ፤
ታስጨርሳላችሁ ፡ ወገንን ፡ በሙሉ ።
አሳብ ፡ ያለው ፡ ይሥራ ፡ አሳቡን ፡ ይፈጽም ፤

ወንድም፡ከወንድሙ፡እየተባበረ፡ከሠራ፡አንድነት፤
አምናለሁ ፡ እንዲያገኝ ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ።
ግን ፡ የኛ ፡ ወገኖች ፡ እንደምታውቋቸው ፤
ተንኰለኞችና ፡ ከዳተኞች ፡ ናቸው ።
እንኳን ፡ እሮማ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ሊያነሡ ፤
በገዛ ፡ አገራቸው ፡ እየተላቀሱ ፡
ርስ ፡ በራሳቸው ፡ ደም ፡ እያፈሰሱ ፡
ይኸው ፡ እናያለን ፡ መስለው ፡ እንደነሱ ።
ስለዚህ ፡ ወንድሜ ፡ ቅድም ፡ እንዳልከው ፤
አሳብክን ፡ ከፈጸምክ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ፤
ከልብህ ፡ ማሰብክን ፡ አንተ ፡ ከተረዳህ ፡
ሐሳብህ፡ይፈጸም፤በል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳህ ።
በእንዲህ ፡ ያለው ፡ አሳብ ፡ ከገፋህበት ፡
ብትሞትም ፡ አይቆጭ ፡ ላገር ፡ ነጻነት ፡

ብሎ ፡ ሽማግሌው ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ቀኑ ፡ መሽቶ ፤ የመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ሽማግሎቹም ፡ ከየመኝታቸው ፡ ላይ ፡ እንዳረፉ ፡ አንድ ፡ ጋዜጣ ፡ ሻጭ ፡ መጥቶ ፡ ጋዜጣ ፡ አደላቸውና ፡ ሲመለስ ፡ ንባብ ፡ የሚያውቁት ፡ ሲያነቡ ፡ ንባብ ፡ የማያውቁ ፡ ሥዕሉን ፡ በመመልከት ፡ እየተደነቁ ፡ ሲያስተውሉ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ሲያስበው ፡ የነበረውን ፡ የቈራጥነት ፡ ተግባር ፡ የሚያሳስበው ፡ ከጋዜጣው ፡ ስላጋጠመው ፡ ለሽማግሎቹ ፡ እየተረጐመ ፡ ያስረዳቸው ፡ ዝመር ። የጋዜጣውም ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ፤ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ ሣህሉ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ አገልጋይና ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወላጅ ፡ ከሆነው ፡ እንግዶኛው ፡ ቤት ፡ እሱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ሄደና ፡ ተንጋደኛው ፡

ጋራ ፡ ተገናኝተው ፡ የየግል ፡ ጕዳያቸውን ፡ ከተጨዋወቱ ፡ በኋላ ፡ ኢጣልያዊ ፡ ሰውዬ ፡ አንድ ፡ ምኒልክ ፡ የተባለች ፡ ውሻውን ፡ ጠራና ፤ ሰሙ ፡ ወይ ፡ ጌታ ፡ እዩዋት ፡ የኔ ፡ ውሻ ፡ መልኳ ፡ አንበሳ ፡ ትመስላለች ፡ ስሟንም ፡ ምኒልክ ፡ ብዬ ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያት ፡ ጥቍሮችን ፡ ከመናቅ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ መልኳም ፡ ሐበሻን ፡ ትመስላለች ፡ በማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ባበሻ ፡ መካከል ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ትችላለች ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ እሳቸውም ፡ እንዴት ፡ በስመ ፡ ጥሩ ውና ፡ በጀግናው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቴ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ውሻ ፡ ስትጠራ በት ፡ ዝሮዬስ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ይስማ ፤ ዐይኔስ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ይይ ፤ እኔስ ፡ ምን ፡ ዘር ፡ አለኝ ፡ ብዬ ፡ አወራለሁ ፤ ከዚህማ ፡ ሞት ፡ አይሻለኝምን ፡ ብለው ፡ ከኪሳቸው ፡ ሽጕጥ ፡ መዘ ው ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ተናግረው ፡ መዥመሪያ ፡ ሰው ዬውን ፡ በኋላ ፡ ውሻውን ፡ ገደሉት ። የሳቸውም ፡ ንግግር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

የዐድዋውን ፡ ጀግና ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ ዳኛው ፡ ምኒ ልክን ፡ በጠላት ፡ አንደበት ፡ ሲዘለፍ ፡ አልሰማም ፤ በሞቴ ፡ ቈርጫለሁ ፡ ብለው ፡ ይህን ፡ ወንጀል ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ታስረው ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ይገኛሉ ። ዕድሜያቸውም ፡ የ፷ ፡ ዓመት ፡ ሽማ ግሌ ፡ ይሆናሉ ፡ ብሎ ፡ ዘርዓይ ፡ ካስረዳቸው ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ መንፈስ ፡ የሚያነቃቃ ፡ ቃል ፡ ይነግራቸዋል ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

ስማችሁ ፡ እናንተ ፡ የኔ ፡ ወገኖች ፡
ጀግናው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሠራውን ፡ ተምች ።
ይህ ፡ ጀግናው ፡ ሰውዬ ፡ የስድሳ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡

ደሙ ፡ ቢፈላና ፡ እጅግ ፡ ቢነደው ፡
ይህን ፡ ግፈኛ ፡ ሰውዬ ፡ በሽጉጥ ፡ አለው ።
እኔም ፡ የማስበው ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
በታሪክ ፡ ገበያ ፡ ገድሎ ፡ ለመሞት ፤
አስቧል ፡ መንፈሴ ፡ በጣሙን ፡ ከፍቶት ።
እሱው ፡ በሰጠኝ ፡ ሰይፍ ፡ እሱን ፡ ቈራርጬ ፡
የኢትዮጵያን ፡ ታሪኳን ፡ ጨብጬ ፡
እሞትላታለሁ ፡ በታሪክ ፡ ገበያ ፡
በሮማ ፡ ከተማ ፡ አስተምሬ ፡ ሙያ ፡
ለውዷ ፡ ሀገሬ ፡ ለኢትዮጵያ ።
በተቻለው ፡ መጠን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ካልሠራ ፡
እየተጨመረ ፡ ይመጣል ፡ መከራ ።
ንጉሣችን ፡ እዚያ ፡ በዓለም ፡ ሸንጎ ፡ ላይ ፡
ስለኢትዮጵያ ፡ መከራውን ፡ ሲያይ ፡
በሰፊው ፡ ሲያስረዳ ፡ የጠላትን ፡ ትዕቢት ፡
ይሰማናል ፡ ይኸው ፡ ዝናው ፡ ዕለት ፡ በዕለት ።
እንደዚህ ፡ ሲደክም ፡ ጠቅል ፡ ለባንዲራው ፡
ለምንድነው ፡ እኛ ፡ የማንረዳዳው ።
እንሙት ፡ እንሥራ ፡ ለሀገር ፡ ለባንዲራ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚሄዱበት ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተቃረበ ፡ እነሱ ፡ ወዳሉበት ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ በሩን ፡ ይመታና ፡ ተከፍቶለት ፡ ይገባና ፡ የሚከተለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዠመር ።

ወታደሩ ፤ ወደ ፡ ተጓዝንበት ፡ ልንደርስ ፡ ነው ፡ አሁን ፡
ጥቂት ፡ ኪሎ ፡ ሜትሮች ፡ ነው ፡ የሚቀሩን ፤

ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ የአገር ፡ ልብሳችሁን ፡
ተነሥታችሁ ፡ አሁን ፡ እንድትለብሱ ፡ ይሁን ።

ካላቸው ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ያንን ፡ ለወዳጁ ፡ እንዲሰጥለት ፡ የተላከውን ፡ ሰይፉንና ፡ ጦር ፡ ጋሻ ፡ ጐፈር ፡ ይለብስና ፡ አንድ ፡ መስተዋት ፡ እየተመለከተ ፡ በፈገግታ ፡ በልብሱ ፡ ማማር ፡ ከመደሰቱ ፡ የተነሣ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

የጀግኖች ፡ ምልክት ፡ የአባቶቼ ፡ መልክ ፡
የነዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የነምኒልክ ፡
በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ሆነሽ ፡ አየሁሽ ፡
በታሪክ ፡ ገበያ ፡ ታኰሪኛለሽ ።

እያለ ፡ ልብሳቸውን ፡ እንደ ፡ ለበሱ ፡ ሲጓዙ ፡ ከመርከቡ ፡ ወደብ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ወርደው ፡ በዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ መሪነት ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ አደባባይ ፡ ጕዟቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ማረፊያ ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ እዚያው ፡ አደሩና ፡ በማግስቱ ፡ በዓሉ ፡ የሚከበርበት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በመጡበት ፡ አኳኋን ፡ በዓሉ ፡ ወደሚከበርበት ፡ አደባባይ ፡ ሄዱ ፤ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ በጠላት ፡ ተማርኮ ፡ ከዋናው ፡ አደባባያቸው ፡ በታች ፡ ጥለውት ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ መሬት ፡ አንጥፈውት ፥ ሲያፌዙና ፡ ሲያንጓጥጡት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋናው ፡ ምልክቷ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ? ኢትዮጵያዊ ፡ ማለትስ ፡ ይኸ ፡ አይደለምን ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ የሚሉት ፡ ይህ ፡ አይደለምን ? በማለት ፡ ወደሱ ፡ እየተጠጉ ፡ ባንጓጠጡት ፡ ጊዜ ፡ እሱም ፡ ላገሩ ፡ ተቈርቍሮና ፡ ደሙ ፡ ፈልቶ ፡ ማን

ንም ፡ ሳይፈራ ፡ በሰልፍ ፡ መካከል ፡ አቋርጦ ፡ ሄዶ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማው ፡ አጠገብ ፡ ወደቀና ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ በሐውልቱ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አገኘበት ።

«ታሪክ ፡ አይደመሰስም » ፡
«መታሰቢያ ፡ አይማረክም » ፡

ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ላገር ፡ ፍቅርና ፡ ታሪክ ፡ በመቈርቈሩ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ አንገቱን ፡ አቅንቶ ፡ ተናገረ ።

ኢትዮጵያ ፡ እንደሆን ፡ ጸሎተኛ ፡ ናት ?
ምነው ፡ ፈጣሪዬ ፡ ይቅር ፡ ብትላት ፤
ልጆቿም ፡ ቢያጠፉ ፡ እሷን ፡ አትበድላት ።
እኔም ፡ እሞታለሁ ፡ ለነጻነት ፡ ለክብር ፡
በጠላት ፡ ከተማ ፡ ሰይፍ ፡ በመሰንዘር ።
ሕይወቱ ፡ ከሚያልፍ ፡ እንዲሁ ፡ በዐጉል ፡
ባለታሪክ ፡ ሆኖ ፡ መሞት ፡ ይሻላል ።
ስለዚህ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እኔን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፥
ዳግመኛ ፡ ውርደትን ፡ በዐይኔም ፡ አታሳየኝ ፤
ዛሬውኑ ፡ እንድሞት ፡ አንተው ፡ ፍቀድልኝ ።
የወንድሞቼን ፡ ደም ፡ ደመወዝ ፡ እበላለሁ ፡
በዓለ ፡ ክብር ፡ ሆኜ ፡ ይኸው ፡ እታያለሁ ።
እኔን ፡ የመረረኝ ፡ ያንገፈገፈኝ ፡
ሮማ ፡ አምጥተው ፡ ውርደት ፡ ሲያሳዩኝ ፤
እመሬት ፡ ጥለውት ፡ መታሰቢያችንን ፡
እኛን ፡ አስመጥተው ፡ ተመልከቱ ፡ ሲሉን ።

ይህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ ውርደቷ ፡ ነው ፤
እባክህ ፡ አምላኬ ፡ ይቅር ፡ ብትል ፡ ምነው ።
ማጥፋቱን ፡ እንደሆን ፡ በጣም ፡ አጥፍተናል ፤
አለመተባበር ፡ እዚህ ፡ አድርሶናል ።
አለመተባበር ፡ የሚያመጣው ፡ ጣጣ ፡
ይኸው ፡ ተቀበልን ፡ ውርደት ፡ ከባላንጣ ።

እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ሲማረር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ሲሮጥ ፡ ይመጣና ፡ እንዲነሣ ፡ ቢጠይቀው ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ በድፍረትና ፡ በኃይል ፡ መለሰለት ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

እንዴት ፡ ይንገላታል ፡ የኛ ፡ መታሰቢያ ፡
የውዱ ፡ ሀገሬ ፡ የኢትዮጵያ ።
የሀገሬ ፡ ምልክት ፡ የሀገሬ ፡ መልክ ፡
እንዴት ፡ እዚህ ፡ ይውደቅ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ።
እሱ ፡ ወድቆ ፡ ከማይ ፡ እኔ ፡ እወድቃለሁ ፤
ሕይወቴን ፡ ለክብሬ ፡ እሰዋለሁ ።
በየጦር ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ ድል ፡ ያደርጋል ፤
ግን ፡ እንደ ፡ ሮማ ፡ ሕዝብ ፡ መቼ ፡ ይባልጋል ፥
ግፍ ፡ በግፍ ፡ ላይ ፡ መሥራት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ብሷል ፤
እንዴት ፡ መታሰቢያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ይጣላል ፥
ላስተዋይ ፡ ኀሊና ፡ በጣም ፡ ያስገርማል ።
ሲሆን ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ይቀመጣል ፡ እንጅ ፡
እንዴት ፡ ይዋረዳል ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ደጅ ።
ትሰሙኝ ፡ እንደሆን ፡ ይልቅ ፡ ልምከራችሁ ፤
በክብር ፡ አስቀምጡት ፡ በሥራት ፡ አድርጋችሁ ።

ይኸን ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ፋሺስቶች ፡ በጣም ፡ እያፌዙ ፡ ይሥቁበት ፡ ዠመር ፤ ይልቁንም ፡ አንድ ፡ የፋሺስት ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ አንጓጠጠው ።

የሮማው ፡ ጦር ፡ መኰንን ።

ሰማህ ፡ ወይ ፡ ወዳጄ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ደፋር ፡ ነህ ፤
ደፍረህ ፡ ስትናገር ፡ ደግሞ ፡ አለማፈርህ ።
ክብራችሁም ፡ ይኸው ፡ የምናየው ፡ ነው ፥
ከኛ ፡ እጅ ፡ የማይወጣ ፡ የታሰረ ፡ ነው ፤
መሣሪያችሁም ፡ ይኸው ፡ ከራ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡
ጠላት ፡ የማይጐዳ ፡ ኃይል ፡ እንኳ ፡ የሌለው ።
መልካችሁም ፡ ይኸው ፡ እንደምናያችሁ ፡
ከኛ ፡ የተለያችሁ ፡ ጥቋቍሮች ፡ ናችሁ ፥
ይኸው ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የናንተ ፡ ክብራችሁ ፤
ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ አየናችሁ ።
ከዚህ ፡ ዞር ፡ በል ፡ ሂዳ ፡ እንዲያ ፡ ወደዚያ ፡
እንዳትዋረድ ፡ በታሪክ ፡ ገበያ ፤

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

በኢትዮጵያዊነቴ ፡ እኔ ፡ አላፍርበትም ፤
ብኰራ ፡ እችላለሁ ፡ በየሄድኩበትም ።
የሚዋረደውን ፡ እግዜር ፡ ነው ፡ የሚያውቀው ፤
ይልቅስ ፡ ተመልከት ፡ ታሪክ ፡ ሊሠራ ፡ ነው ።
የዛሬዋ ፡ ቀንስ ፡ ባለታሪክ ፡ ነሽ ፤
እንዴት ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡ ታሰሚኛለሽ ።
መልካም ፡ ነው ፡ አሳብህ ፡ ዞር ፡ በል ፡ ካልከኝ ፡
ክብሬን ፡ አሳይቼ ፡ ማለፍ አለብኝ ፤

ባለጌ ፡ አልምሰልህ ፡ በጣም ፡ ሥልጡን ፡ ነኝ ።
እንግዲህ ፡ ላሳይህ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርክር ፡
በየጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሰይፍ ፡ አሰነዛዘር ።
አምላክ ፡ ተቄጥቶ ፡ በግፍ ፡ ተሸፍነን ፡
እመሬት ፡ ተጥለን ፡ ልንቀር ፡ ተወርውረን ፧




ከጠላቴ ፡ ጋራ ፡ ደልቶኝ ፡ ከምኖር ፡
ሞትን ፡ እመርጣለሁ ፡ ለሀገሬ ፡ ክብር ።

ለክብሬ ፡ እሞታለሁ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቴ ፡
ሕይወቴ ፡ ትለወጥ ፡ ስለ ፡ ነጻነቴ ፤

ብሎ ፡ ሰይፍ ፡ መዞ ፡ በመዠመሪያ ፡ ያንን ፡ ተነሣ ፡ ያለውን ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ አንገቱን ፡ ቈርጦ ፡ ይጥልና ፡ በደም ፡ የተነከረውን ፡ ባለሙጣ ፡ ሰይፍ ፡ መዞ ፤ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ እየፎከረ ፡ የኢዮጋሊያን ፡ መታሰቢያ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ አድርጓት ፡ ዋለ ። ጠላትን ፡ በገዛ ፡ አደባባዩ ፡ እያባረረ ፡ በሰይፍ ፡ ሲገርፈው ፡ የዚያን ፡ ዕለት ፡ የነበሩትን ፡ ጋዜጠኞች ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለዋውጦት ፡ ነበር ።

የጀግናው ፡ ፉከራም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፤
ዘርዓይ ፡ የጠቅል ፡ አሽከር ፡
የተሰናዳው ፡ ለሀገሩ ፡ ክብር ፤



የጠቅል ፡ አሽከር ፡ የንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡
በሰው ፡ ከተማ ፡ ወንድ ፡ አስከባሪ ።

ዘርዓይ ፡ የወንዶች ፡ ወንድ ፡

ሮማ ፡ ገብቶ ፡ ፋሺሽት ፡ የሚያጫድ ፡

እያለ ፡ የሚያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ሲያርድ ፡ ሕዝቡ ፡ በ ያለበት ፡ ሲበተን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አንጥፈውት ፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን ፤ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ አንሥቶ ፡ ሐውልቱን ፡ ካ ከናነበው ፡ በኋላ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ወርዶ ፡ እንዳበደ ፡ ሰው ፤ በሰ ልፉ ፡ መካከል ፡ እየሮጠ ፡ ብዙ ፡ ጠላቶቹን ፡ ይፈጅ ፡ ዠመር ።

እንደዚህ ፡ በለው ፡ ጀግንነት ፡ ያገሩን ፡ ክብር ፡ ካሳወ ቀ ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ጕልበት ፡ ምንም ፡ ኀይለኛ ፡ ቢሆ ን ፡ ዘዴና ፡ ማሸነፊያ ፡ ስለማይታጣለት ፡ በጥይት ፡ አቍስለ ን ፡ እንይዘዋለን ፡ በማለት ፡ ጸጥታውን ፡ የሚያስከብሩ ፡ ፖ ሊሶች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲታኰሱ ፡ ከሰልፉ ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጨረሱ ።

እሱ ፡ ግን ፡ የዠመረውን ፡ ዐላማ ፡ እስከ ፡ መጨረ ሻው ፡ አደርሳለሁ ፡ በማለት ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ታሪኬን ፡ አሳምሬ ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ ተስፋ ፡ አልቈርጥም ፡ ብሎ ፡ በ ዐቀደው ፡ ዐላማ ፡ ሲገማለል ፡ ተባራሪ ፡ ጥይት ፡ ስድስት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ መታውና ፡ ስላቈሰለው ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ አይተው ፡ ሰይፉን ፡ ለመቀማት ፡ ሲጠጉት ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ከተከ ራከረ ፡ በኋላ ፡ ሰይፉን ፡ ቀምተው ፡ ጀግናውን ፡ እያንገላቱ ፡ ወደ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ያቀርቡታል ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

ሙሶሊኒ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ።


ሰማህ ፡ ወይ ፡ አንተ ፡ ልጅ ፡ እስቲ ፡ ልጠይቅህ ፤

አሁን ፡ አንተን ፡ እኔ ፡ እዚህ ፡ ያስጠራሁህ ፡

ከገናናው ፡ ፊቴ ፡ እንድትቀርብ ፡ ያረግሁህ ፡
አስቢያለሁና ፡ ጥያቄ ፡ ልሰጥህ ።
እኔን ፡ ሳትፈራ ፡ በሙሉ ፡ አንደበት ፡
ጠብ ፡ ያነሣህበትን ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡
ምስጢሩን ፡ በሙሉ ፡ እኔ ፡ ስጠይቅህ ፡
ያለድንጋጤ ፡ ያለፍርሀት ፡ ዘርዝረህ ፡
በቀጥታ ፡ ለኔ ፡ ማስረዳት ፡ አለብህ ? ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

መልካም ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ እሺ ፡ ልንገርዎ ፡
ከፈቀደልኝስ ፡ ክቡርነትዎ ።



የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ በአደባባያችሁ ፡ ላይ ፡
ሲንገላታ ፡ አየሁት ፡ መከራውን ፡ ሲያይ ።
ስለዚህ ፡ እኔም ፡ ተጠግቼ ፡ ብመለከተው ፡
ዐይኔንም ፡ ከፍቼ ፡ ቆሜ ፡ ባስተውለው ፡

እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ ነው ።
የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ አይደመሰስም ፡
ለጊዜው ፡ ሳይሆን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፤
የይሁዳን ፡ አንበሳ ፡ ጠላት ፡ አይማርክም ።
ለአገሬ ፡ ታሪክ ፡ እሞትላታለሁ ፡ እስኪወጣ ፡ ነፍሴ ፤
ይህም ፡ ቃል ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ቀ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
የሚለውን ፡ ታሪክ ፡ አነበብኩትና ፡
ሕይወቴን ፡ ለክብሬ ፡ መረጥኩ ፡ ይኸውና ።
ተናገር ፡ ስላሉኝ ፡ ይኸው ፡ ተናገርሁ ፤
ፍርዴን ፡ እንድቀበል ፡ እጠብቃለሁ ።

ሙሶሊኒ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ከመናደዱም ፡ በላይ ፡ እየማቀ ፡ ከመቀመጫው ፡ ላይ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ እኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ የሚያደርገው ፡ መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ በትዕቢት ፡ አነጋገር ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይዘልፈው ፡ ዠመር ።

እንዴት ፡ ያለው ፡ ደፋር ፡ በጣም ፡ ዐይን ፡ አውጣ ፡ ነው ፤
እሱ ፡ የሚያስበው ፡ እኔ ፡ እንድገለው ፡ ነው ።
አንተን ፡ የሚያኽል ፡ ሽፍታ ፡ አሁን ፡ ከሞትህ ፡
ትልቅ ፡ ጀግንነት ፡ ነው ፡ ለአንተ ፡ የሚሰማህ ።
ደማችን ፡ መች ፡ ወጣ ፡ አንተ ፡ ከሞትክማ ፤
ሥቃይ ፡ ይገባሃል ፡ ዓለም ፡ እስኪሰማ ።
ዛሬ ፡ አንተን ፡ ብገልህ ፡ ሡራት ፡ ይሰማሃል ፤
ሥቃይን ፡ ማሳየት ፡ ለአንተ ፡ ይገባሃል ።
ላሻሻትህ ፡ እስቲ ፡ መላ ፡ እንፍጠርለት ፤
በጣም ፡ ይገባሃል ፡ ሥቃይን ፡ ማሳየት ።
(በቍጣ) ፤ ኑ ፡ ወታደሮች ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀበሉ ፡
እፊቴ ፡ ያላችሁ ፡ ለጊዜው ፡ በሙሉ ።

ይህን ፡ ዐመፀኛ ፡ ተንኰለኛ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ሰው ፡
ከሲሲል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ ማሰር ፡ ነው ፤
እዚያ ፡ ውሰዱና ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡
አሁኑን ፡ ዛሬ ፡ በጥብቅ ፡ እሰሩት ፡፡
ከታሰረም ፡ ወዲያ ፡ እስረኛው ፡ በጥብቅ ፡
ሰውም ፡ እንዳያየው ፡ እንዳይጠየቅ ፡፡
ችግር ፡ ሲበዛበት ፡ ባሳር ፡ በመከራ ፡
በቀን ፡ አንድ ፡ ዳቦ ፡ በውሃ ፡ ተነክሮ ፡
ከተነከረም ፡ ወዲያ ፡ በውሃ ፡ ዳቦው ፡
እያስገደዳችሁ ፡ በግድ ፡ ይብላው ፡፡
ምናልባት ፡ ሲያመልጥ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆን ፡
በጥብቅ ፡ በሥቃይ ፡ እንዲገደል ፡ ይሁን ፡፡
በሉ ፡ ውሰዱልኝ ፡ ከዚህ ፡ ካጠገቤ ፡
ፍርዴ ፡ ተፈጽሟል ፡ በሙሉ ፡ አሳቤ ፡፡

ብሎ ፡ ሙሶሊኒ ፡ ፍርዱን ፡ ሲወስን ፡ ጀግናው ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ እንደዚህ ፡ በሆን ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ ፍርዱ ፡ ደሙ ፡ ፈልቶ ፡ ባራት ፡ ወታደሮች ፡ የፊጥኝ ፡ ተይዞ ፡ የነበረው ፡ ቀስለኛ ፡ ቀስሉን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ሳይቈጥረው ፡ እንዲያውም ፡ የሙሶሊኒ ፡ መንደላቀቅ ፡ እጅግ ፡ ስላናደደው ፡ አራቱን ፡ ወታደሮች ፡ ለመንጠቅ ፡ እየተናነቀ ፡ ቢያቅታቸው ፡ ከውጭ ፡ ሌላ ፡ ረዳት ፡ ተጠርቶ ፡ ጀግናውን ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስን ፡ ያዙትና ፡ ቆሙ ፡፡

ሙሶሊኒም ፡ በጀግንነቱ ፡ ከመደነቁ ፡ የተነሣ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይናገር ፡ ጀመር ፡፡

ሙሶሊኒ ፡፡

አንድ ፡ ወንበዴ ፡ ሽፍታ ፡ መያዝ ፡ አቅቷችሁ ፡
አንድላንድ ፡ እንኳ ፡ አይደል ፡ አራት ፡ ሆናችሁ ፡

ሊገለኝ ፡ ነበር ፡ ነጥቆ ፡ ሊያመልጣችሁ ።
የአሁኑ ፡ አይብስም ፡ ወይ ፡ ስናመዛዝነው ፡
እኔን ፡ የደፈረኝ ፡ እንዴት ፡ ቢንቀኝ ፡ ነው ።
ገብቶኛል ፡ ሐሳብህ ፡ ያንተ ፡ ምኞት ፡ ለኔ ፡
ትዕቢተኛ ፡ ጨካኝ ፡ ዐይን ፡ አውጣ ፡ አረመኔ ።
ዡርሮህ ፡ አይሰማም ፡ ወይ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ እባክህ ፡
ሙሶሊኒ ፡ ሲባል ፡ ሲወራም ፡ አልሰማህ ።
አታውቀኝ ፡ እንደሆን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዕወቀኝ ፤
የፋሺስቶች ፡ መሪ ፡ ሙሶሊኒ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።
አስተዋይ ፡ ነህ ፡ ብለን ፡ መርጠን ፡ ብናመጣህ ፡
እኔን ፡ ለማዋረድ ፡ ዳግመኛ ፡ ማሰብህ ።
እንዴት ፡ ያለውን፡ ልብ ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የያዝከው ፡
ለሚሰማ ፡ ሁሉ ፡ የሚገርም ፡ የሚደንቅ ፡ ነው ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

ይልቅስ ፡ የሚገርም ፡ የርስዎ ፡ ትዕቢት ፡ ነው ፡
በጭካኔ ፡ በግፍ ፡ የሰው ፡ አገር ፡ ወረው ፤
መቃሰቢያችንን ፡ አሽናፈው ፡
የደሀዳን ፡ አንበሳ ፡ ድል ፡ አድራጊውን ፡
መሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሰደቅ ፡ ዓላማችን ፡
በግፈኛው ፡ መንግሥት ፡ በርስዎ ፡ ዘመን ።
ደግሞ ፡ ሲናገሩ ፡ አለማፈርዎ ፥
ክብር ፡ አለኝ ፡ እያሉ ፡ ለኔ ፡ ማውራትዎ ፤
ከፈቀዱልኝስ ፡ ክቡርነትዎ ፡
የፋሺስቶችን ፡ ክብር ፡ እኔ ፡ ልንገርዎ ፤
አንበሳና ፡ ተኵላን ፡ አንድነት ፡ ቢያይዋቸው ፡

በክብር ፡ የሚበልጡ ፡ ማንኛቸው ፡ ናቸው ።
የርስዎ ፡ ምሳሌ ፡ ተኵላ ፡ ስትሆን ፤
እኔም ፡ አላፍርበት ፡ አበሳ ፡ ብሆን ።

ሙሶሊኒ ፤ እኔ ፡ አግኝቼዋለሁ ፡ ያንተ ፡ አሳብ ፡ በእውነት ።
እንዲህ ፡ ስትናገር ፡ በሙሉ ፡ አንደበትህ ፡
ቈርጠሃል ፡ ለሞት ፡ እንደ ፡ አስተያየትህ ።
እኔ ፡ አንተን ፡ ገድዬ ፡ ስሜን ፡ አላጠፋም ፤
ለጊዜው ፡ ሳይሆን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡
እስራት ፡ ይሻላል ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ።
እስር ፡ ቤት ፡ ውሰዱት ፡ ዐይኔም ፡ አይየው ፤
ራሱ ፡ የዘረ ፡ ጭራሽ ፡ እብድ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

በሙሶሊኒ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ጀግናውን ፡ ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ሲሲል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ይወስዱታል ፤ ጀግናውም ፡ በስር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይተክዛል ።

ቍስለኛው ፡ ወታደር ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ እስረኛው ፤
ቍስሌን ፡ ያከሙኝ ፡ በደም ፡ አጨማልቀው ፡
ያለርኅራሄ ፡ በጭካኔ ፡ አስረው ፤
አሳቤ ፡ ሳይሞላ ፡ እዚህ ፡ ልቀር ፡ ነው ።
የሲሲል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ የጀግኖች ፡ መኖሪያ ፤
የሚታሰርብሽ ፡ ጀግና ፡ ባለሙያ ።

በትካዜ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ውዲቷ ፡ ለምለሟ ፡ አገሬ ፡
ትሰሚኝ ፡ እንደሆን ፡ ልላክልሽ ፡ ወሬ ።
ውዲቱ ፡ አገሬ ፡ ውቧ ፡ ኢትዮጵያ ፡
በሮማ ፡ ከተማ ፡ ተሠራልሽ ፡ ሙያ ።

እንደዚህ ፡ እያለ ፡ አገሩን ፡ በመናፈቅና ፡ በሙሉ ፡ ትዝታ ፡ ሲናፍቅ ፡ ቀኑ ፡ ይመሽና ፡ ከተኛ ፡ በኋላ ፡ በመኝታው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ እንዳለ ፡ በእንቅልፍ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ እሱን ፡ የሚጠብቀው ፡ ወታደር ፡ ሲንጐራደድ ፡ ዘርዓይም ፡ በእንቅልፍ ፡ ተውጦ ፡ እንደተኛ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ተልኮ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያጽናናዋል ፡፡

በሠራኸው ፡ ሥራ ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፤
ላንተ ፡ እንድገልጽህ ፡ ተልኬአለሁ ፡ መልክት ፡፡
በድል ፡ ሊገባ ፡ ነው ፡ ነጻነት ፡ መሥርቶ ፤
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአምላኩ ፡ ተመርቶ ፡፡
አንተም ፡ እንደሆንክ ፡ በፈጸምከው ፡ ታሪክ ፡
ክብርን ፡ ትወርሳለህ ፡ በአባቶችህ ፡ መልክ ፡፡
ፋሺስት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሠራችው ፡ ግፍ ፡
ለአገርህ ፡ ተከፈለ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ዕጥፍ ፡፡
ወደ ፡ ፊትም ፡ ቢሆን ፡ ይፈረድባታል ፤
የአገራችሁ ፡ ወሰን ፡ በሙሉ ፡ ይስፋፋል ፡፡
በእጅዋ ፡ የነበረውን ፡ አገር ፡ ትለቃለች ፤
መታሰቢያችሁን ፡ ትመልሰዋለች ፡፡
አንተም ፡ ስለ ፡ ክብሯ ፡ ለሞትክላት ፡
ታውቀህ ፡ ትኖራለህ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ፊት ፡፡
የኔ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለም ፡ አዳምጠኝ ፡ በምር ፡
እሱ ፡ ነው ፡ የላከኝ ፡ ይህንን ፡ ምስጢር ፤
የኃያሎች ፡ ኃያል ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡፡
በርታ ፡ አስብ ፡ ጠንክር ፡ በጸሎትህ ፤
ለወገን ፡ መመኪያ ፡ መኵሪያ ፡ ትሆናለህ ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘርዓይ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ብድግ ፡ ይልና ፡ ሌሊት ፡ ሲታየው ፡ በደረው ፡ ሕልም ፡ እየተደነቀ ፡ ተመስገን ፡ አምላኬ ፡ ተመስገን ፡ ፈጣሪዬ ፡ ጨለማውን ፡ ወስደህ ፡ ብርሃኑን ፡ ያመጣህ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተመሰገንክ ፡ ሁን ፡ ዳግም ፡ ሌሊት ፡ በሕልሜ ፡ ሳየው ፡ ያደርኩትን ፡ እስቲ ፡ እውነት ፡ አድርገው ፡ አለና ፡ ፈጣሪውን ፡ ካመሰገነ ፡ በኋላ ፡ እየተደሰተ ፡ ያገሩን ፡ ነጻነት ፡ መመለስ ፡ ከአምላክ ፡ በተሰጠው ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ ይጠባበቅ ፡ ዠመር ።

ክፍል ፡ ፳ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ እዋናው ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ ከጥንት ፡ ክብሩ ፡ ላይ ፡ ተመለሰ ። አሸናፊው ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ አደባባዩ ፡ በጥንት ፡ ክብሩ ፡ ላይ ፡ መመለሱ ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ደስታ ፡ ስለ ፡ ተሰማው ፡ ሴቱ ፡ በእልልታ ፡ ወንዱ ፡ በጭብጨባ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ካህናቱ ፡ በጸሎት ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ በማመስገን ፡ ደስታቸውን ፡ ገልጠው ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ የነበሩት ፡ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ አርበኞች ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ እየቀረቡ ፡ ደስታቸውን ፡ ገለጡ ፤ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከጃንሆይ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ የሚከተለውን ፡ ይናገራል ።

እሰይ ፡ ዓለሜ ፡ መጣኽልኝ ፡
እሰይ ፡ መኵራዬ ፡ መጣኽልኝ ፡

ልጆቼን ፡ ያረደው ፡ እኔን ፡ ሳያርደኝ ፤
ከብቶቼን ፡ የበላው ፡ እኔን ፡ ሳይበላኝ ።
እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣህ ፡ የነጻነት ፡ ጌታ ፤
የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይመጣ ፤
ጠቅል ፡ ከዙፋንህ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አትታጣ ፡

ይሉና ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ይመለሳሉ ። አንድ ፡ አርበኛ ፡ ጐፈ ርና ፡ አንፋሮ ፡ ለብሶ ፡ መንታ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ሰይፍ ፡ ታጥቆ ፡ ጋሻውን ፡ አንግበ ፡ ሰይፉን ፡ በእጁ ፡ እየነቀነቀ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንጐራደደ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ የደስታ ፡ መግለ ጫውን ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ በቀረርቶ ፡ ያሰማ ፡ ዝመር ።

ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ መድኀኒተ ፡ ዓለም ፤
ክብሩ ፡ ተገለጠ ፡ በመላው ፡ ዓለም ።
እናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አለሽ ፤
ተመልሰሽ ፡ ታየሽ ፡ በጥንት ፡ ክብርሽ ።
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጠቅል ፡ ብርታት ፡
ታላቅ ፡ ክብር ፡ ያገኘች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናት ።
ጣልኳት ፡ ያለው ፡ ወድቆ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስትቆም ፡
ያልደነቀውና ፡ ያልገረመው ፡ የለም ።
እስቲ ፡ ላነሣሣው ፡ የጀግኖችን ፡ ሥራ ፡
ለክብር ፡ የሞቱትን ፡ በሃይማኖት ፡ ካራ ።
በጭካኔ ፡ ሞተ ፡ በከባድ ፡ መትረየስ ፡
እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሐዋርያው ፡ ጴጥሮስ ።
መትረየስ ፡ ዘርግተው ፡ ተመልከት ፡ ሲሉት ፡
አሁን ፡ የት ፡ ይገኛል ፡ መስቀል ፡ የሚመከት ፤
ሃይማኖቱ ፡ ጽኑ ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ብረት ።
ልበ ፡ ሙሉ ፡ ጀግና ፡ አንበሳው ፡ ዘርዓይ ፡
የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ አጠናኸው ፡ ወይ ፤

ሕይወቴ ፡ ለነጻነቴ ፡ ብለህ ፡ የተናገርከ ፡
ባገርህ ፡ ነጻነት ፡ እየተማገረርክ ።
ሮማ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሰይፍ ፡ መዘባቸው ፡
የነሱን ፡ ክብርና ፡ የኛን ፡ ቢያስተውለው ፡
በፍጹም ፡ በጭራሽ ፡ የተለያየ ፡ ነው ፤
ልዩነቱን ፡ እንደሁ ፡ ተመልካች ፡ ያስበው ፤
አንበሳውም ፡ አንበሳ ፡ ተኰላውም ፡ ተኰላ ፡ ነው ።
ሮማ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ አንበሳው ፡ ቢያገሣ ፤
ዓለም ፡ ተደነቀ ፡ ፍጡር ፡ እስከ ፡ እንስሳ ።
ተጕዞ ፡ ሄደና ፡ በሰው ፡ አደባባይ ፡
ይፈርድ ፡ ዠመረ ፡ አንበሳው ፡ ዘርዓይ ።
ጐራዴውን ፡ መዞ ፡ ጀግናው ፡ ቢያንፈራጥጥ ፡
የሮማ ፡ ከተማ ፡ ተይዛ ፡ ዋለች ፡ በምጥ ።
የዚያ ፡ ዕለት ፡ ሮማ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አግኝታ ፡
ስትገረፍ ፡ ዋለች ፡ በሰይፍ ፡ ስትመታ ።
መሬት ፡ ጠቦት ፡ ዋለ ፡ ጀግናውን ፡ በሮማ ፡
ታወቀ ፡ ጀግንነት ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሰማ ።
ሰይፉን ፡ ቢሰነዝር ፡ የጠቅል ፡ አሽከር ፡
ዓለም ፡ አደነቀው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክብር ።
የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ኀይለኛው ፡ ነጋዴ ፡
ባንገት ፡ ተጫወተ ፡ የዘርዓይ ፡ ጐራዴ ፤
የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ እሰው ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡
ሲጐማለል ፡ ዋለ ፡ በሮማ ፡ ተሰማርቶ ።
ተመሰከረለት ፡ የሱ ፡ ታሪክማ ፡
የዘርዓይ ፡ ጀግንነት ፡ በሮማ ፡ ከተማ ።
እኔ ፡ እንኳ ፡ ራሴ ፡ ሳመዛዝነው ፡
እንዴት ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ እጅግ ፡ ደፋር ፡ ነው ።

ያለአንድ ፡ አጋዥና ፣ ያለአንድ ፡ አይዞህ ፡ ባይ ፡
ክብርን ፡ አሳዋቂ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ።
የኢትዮጵያን ፡ ክብር ፡ ዘርዓይ ፡ ተከናንቦ ፡
ሮማ ፡ ላይ ፡ ታየ ፡ በታሪክ ፡ ተከቦ ።
አባ ፡ ጠቅል ፡ ኃይሌ ፡ ነጻነቴ ፡ ሆይ ፡
በጀግናው ፡ መጋደል ፡ ደስ ፡ ብሎሃል ፡ ወይ ፡
ደስ ፡ ብሎሃል ፡ በጣም ፡ አይጠረጠርም ፤
ዓለም ፡ አድንቆታል ፡ ምስክር ፡ አያሻም ።
ሮማ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ሰይፉን ፡ ሲሰነዝር ፡
የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ዋለ ፡ ክብር ።
የዚያን ፡ ዕለት ፡ እርዳታ ፡ አግኝቶ ፡ ቢሆን ፡
፳ ፡ መትረየስና ፡ ብምብ ፡ ምናምን ።
እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ እንደነአብርሃም ፡
ተመልሶ ፡ ነበር ፡ የየካቲት ፡ ደም ።
ዳግም ፡ ባዓድ ፡ በኩል ፡ ስናመዛዝነው ፡
የፈጸመው ፡ ታሪክ ፡ የሚያስገርም ፡ ነው ፡
ላስታዋለውና ፡ ላመዛዘነው ።
ሥራው ፡ ይበቀዋል ፡ የሱ ፡ መጋደል ፤
ያውቁታል ፡ መሪያችን ፡ ገናናው ፡ ጠቅል ።
እስቲ ፡ እናስተውለው ፡ መለስ ፡ ብለን ፡
የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ የዛሬዋን ፡ ቀን ።
እስቲ ፡ እናስተውለው ፡ የእግዜርን ፡ ውለታ ፡
ይኸው ፡ አለበሰን ፡ የነጻነት ፡ ኩታ ።
እግዚአብሔር ፡ አስቦ ፡ እኛን ፡ ይቅር ፡ ሲለን ፡
አገርክን ፡ ነጻ ፡ አውጣ ፡ ጠቅል ፡ ብሎ ፡ ሰጠን ።

ይህን ፡ ካሰማ ፡ በኋላ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ይመለስና ፡ ይቀመጣል ። ደግሞ ፡ አንድ ፡ አርበኛ ፡ በዘርዓይ ፡ ጀግንነትና ፡ በሠ

ራው ፡ የቈራጥነት ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ ተደሰተ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንቈራጠጠ ፥ በገለሌ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያሰማ ፡ ዠመር ።

የጀግኖች ፡ ጀግና ፡ የወንዶች ፡ ወንድ ፡
አንበሳው ፡ ዘርዓይ ፡ የአንበሳው ፡ ክንድ ፡
ሮማ ፡ መካከል ፡ ፋሺስት ፡ የሚያርድ ።
ተጕዞ ፡ ወርዶ ፡ መርከብ ፡ ለመርከብ ፡
የተላከውን ፡ ሰይፍ ፡ የሚያስረክብ ።
ለአገሩ ፡ ክብር ፡ ለንጉሡ ፡ ዝና ፡
ተጕዞ ፡ ሄዶ ፡ እሩቅ ፡ ጐዳና ።
ተሻግሮ ፡ ሄዶ ፡ እሮማ ፡ ድረስ ፡
የጠቅል ፡ አሽከር ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡
ለአገሩ ፡ ክብር ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ።
አርጅቶ ፡ ነበር ፡ ሰይፉ ፡ በሮማ ፤
ጀግናው ፡ ቢመዘው ፡ ክብሩ ፡ ተሰማ ።
መታሰቢያችን ፡ እሮም ፡ ቢያሳ ፡
ባንዲራ ፡ ለብሶ ፡ ሆነና ፡ አንበሳ ።
ሰይፉ ፡ ቢመዘዝ ፡ በዘርዓይ ፡ ክንድ ፡
ተጻፈ ፡ ዝናው ፡ በታሪክ ፡ ዐምድ ።
የዓለም ፡ ጋዜጦች ፡ እንደዚህ ፡ አሉ ፡
በሰፊው ፡ ታሪክ ፡ እየቀጠሉ ።
መታሰቢያዋ ፡ የኢትዮጵያ ፡
ነፍስ ፡ ዘራ ፡ አሉ ፡ በዓለም ፡ ገበያ ።
አርበኞች ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ሞልተዋል ፡
እንዳንተ ፡ ጀግና ፡ ወዴት ፡ ይገኛል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ አርበኛ ፡ ነኝ ፡
እንደሱ ፡ ደፋር ፡ ጀግና ፡ አጣሁኝ ።

ይገርማል ፡ ጃንሆይ ፡ የዘርዓይ ፡ ውለታ ፤
እሮማ ፡ ከተማ ፡ በሰይፍ ፡ የሚማታ ።
እያንበረከከ ፡ ጠላትን ፡ ሲያርደው ፡
ፋሺስት ፡ በረገገ ፡ በገዛ ፡ ከተማው ፤
እያንዳንዳችን ፡ ስናመዛዝነው ፡
እንደ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ጀግና ፡ ላይገኝ ፡ ነው ።

ይልና ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ይናገራሉ ።

ለሀገሩ ፡ ለወገኑ ፡ ደግ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡ በላይኛው ፡
ይከፈለዋል ፡ በዕጥፍ ፡ ውለታው ።
የጀግኖችን ፡ ሥራ ፡ ተመልክተነዋል ፥
እንደየሙያቸው ፡ ይከፈላቸዋል ፤
ጀግናውንም ፡ ቢሆን ፡ አስጠርተነዋል ፥
አገሩ ፡ ሲመጣ ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ።
ስለዚህ ፡ እናንተም ፡ አንድነት ፡ ሁናችሁ ፡
ቂምና ፡ በቀልን ፡ ከልብ ፡ ፍቃችሁ ፡
ለጋራ ፡ አገራችን ፡ መሥራት ፡ አለባችሁ ።
እገሌ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሜን ፡ ገድሎታል ፡
እገሌ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባቴን ፡ ገድሎታል ፡
ደሜን ፡ ሳልበቀል ፡ እንደምን ፡ ይቀራል ፡
በማለት ፡ እናንተ ፡ ሐሳብ ፡ አታድርጉ ፡
በስንፍና ፡ መንገድ ፡ አትፈላለጉ ።
ሥራ ፡ ይዠመራል ፡ ባዲሱ ፡ ዘመን ፤
አንድ ፡ ላይ ፡ ተጋግዘን ፡ መሥራት ፡ አለብን ።
ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሁላችንም ፡
ሳይደርስን ፡ አልቀረም ፡ የመከራ ፡ ደም ።

የመከራን ፡ ጊዜ ፡ የመከራን ፡ ዘመን ፡
እግዜር ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ ካለፍናት ፡ በሐዘን ፡
አንድ ፡ ልብ ፡ ሁነን ፡ መሥራት ፡ ነው ፡ ያለብን ።
ዳግመኛ ፡ በጠላት ፡ እንዳትንገላቱ ፡
ያለፈው ፡ አለፈ ፡ ለወደ ፡ ፊት ፡ በርቱ ።
ልብ ፡ ያለው ፡ ልብ ፡ ያድርገው ፡ ይህንን ፡ ምክር ፡
ዳግም ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዳትወረር ፡
አንድ ፡ እንሁን ፡ እኛ ፡ በመተባበር ።
አለመተባበር ፡ የሚያመጣው ፡ ዕዳ ፡
እስቲ ፡ እናስተውለው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ተጐዳ ፡

አሉና ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ንግግራቸውን ፡ ካቆሙ ፡ በኋላ ፡ ለኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ መልክት ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ ተፈቶ ፡ እንዲመጣ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ይልካሉ ።

## ክፍል ፡ ፱ ።

መላክተኛው ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ይገባል ፤ መልክቱን ፡ ይቀበላል ።

### ግርማዊነታቸው ።

እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ለኢጣልያ ፡ ፋሺስት ፡
በደረሰህ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የኔ ፡ መልክት ፡
አንበሳውን ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስን ፡
በክብር ፡ ተፈቶ ፡ እንዲላክ ፡ ይሁን ።
በክብር ፡ አድርጉና ፡ እንዳይንገላታ ፡
ከሲሲል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ በቶሎ ፡ እንዲፈታ ፡
ለሀገሩ ፡ የሠራውን ፡ ይህን ፡ ባለውለታ ፡
ናፍቃዋለችና ፡ እናቲቱ ፡ ሰምታ ፤


ትጠብቀዋለች ፡ እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡
ለጀግናው ፡ ተጋዳይ ፡ ልትከፍለው ፡ ወረታ ።
ባለሰይፉን ፡ ጀግና ፡ ታሪክ ፡ የሠራውን ፡
በክብር ፡ ተፈትቶ ፡ እንዲመጣ ፡ ይሁን ፤
በልና ፡ ንገረው ፡ በሙሉ ፡ ዘርዝረህ ፤
የኢትዮጵያን ፡ ክብር ፡ አንተም ፡ ታውቀዋለህ ፨
ዘርዝርለት ፡ አንተም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡
የተፈጸመውን ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ።
በዓድዋ ፡ ጦርነት ፡ የተሠራውን ፡
አስታውሰህ ፡ ንገረው ፡ እረስቶት ፡ እንደሆን ።

ክፍል ፡ ፲ ።

መልክተኛው ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ይመለሳል ፤ ወደ ፡ ተላ ከበት ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ይሄዳል ፤ የተላከውን ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ መልክት ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ያስረዳል ።

ከገናናው ፡ መንግሥት ፡ ከድል ፡ አድራጊው ፡
ከኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከባለውለታው ፡
ተልኬያለሁና ፡ መልክት ፡ ልንገራችሁ ፤
በሙሉ ፡ ኅሊና ፡ ስሙኝ ፡ አዳምጣችሁ ።
የኢትዮጵያ ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስን ፡
በፍጥነት ፡ በቶሎ ፡ እንድትልኩ ፡ ይሁን ።
በክብር ፡ አርጋችሁ ፡ ሳይንገላታ ፡
ከሲሲል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ በቶሎ ፡ እንዲፈታ ፡
የሠራውን ፡ ታሪክ ፡ ይህን ፡ ባለውለታ ፡
ናፍቀዋለችና ፡ እናቲቱ ፡ ሰምታ ፤
ለሠራው ፡ ጀግንነት ፡ ልትከፍለው ፡ ወሮታ ።

ባለሰይፉን ፡ ጀግና ፡ ባንገት ፡ ተሜዋቹን ፡
በፍጥነት ፡ ፈትታችሁ ፡ እንድትልኩት ፡ ይሁን ።
በቶሎ ፡ ፈትታችሁ ፡ ብትልኩ ፡ ይሻላል ፤
በሱ ፡ የተነሣ ፡ በሕግ ፡ ይጠየቃል ።



ጀግናው ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ የጀግንነቱን ፡ ተግባር ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በቢሲል ፡ ወህረ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ይታያል ።

ረስታችሁ ፡ እንደሆን ፡ አስታውሱ ፡ ታሪክ ፡
የተፈጸመውን ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ።
ገናናው ፡ መንግሥቴ ፡ ይህን ፡ ስለላከኝ ፡
መልክቴን ፡ ፈጽሜ ፡ መልሱን ፡ ጠባቂ ፡ ነኝ ።

ብሎ ፡ ንግግሩን ፡ ካቆመ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ቈይ ፡ ተብሎ ፡ ውጭ ፡ ሲወጣ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ተሰብስቦ ፡ እንደ ዚህ ፡ እያሉ ፡ ይማከራሉ ።

እንዱ፡አማካሪ፤ የቀረው፡ስ ፡ እንኳ ፡ ጕዳት ፡ አላመጣ ፤
የኢጣልያ ፡ ፖሊቲካ ፡ ዛሬ ፡ በጕድ ፡ ወጣ ።
ይህን ፡ እስረኛ ፡ ሰው ፡ ፈትተን ፡ ከላክንማ ፡
ምስጢራችን ፡ ሁሉ ፡ በዓለም ፡ ተሰማ ።
ስለዚህ ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ዘዴ ፡ እንፈልግለት ፡
የኛ ፡ መማክርቶች ፡ ሁላችሁ ፡ ባንድነት ፡
ባልታወቀ ፡ ዘዴ ፡ በቶሎ ፡ እንዲሞት ፡

ይልና ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ አንደኛው ፡ አማካሪ ፡ ዳግም ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ አሳቡን ፡ ይገልጻል ።

ሰው ፡ ተንኰል ፡ ካሰበ ፡ ምንም ፡ አያቅተው ፤
በጣም ፡ ታሻል ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ እስረኛ ፡ ሰው ፡
ከስር ፡ ቤት ፡ አውጥቶ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ማግባት ፡ ነው ።
ከገባ ፡ በኋላ ፡ ዘርዓይ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡
ሐኪሞችን ፡ ጠርቶ ፡ ሰብስቦ ፡ ባንድነት ፡
ምክር ፡ ማካፈል ፡ ነው ፡ በመርፌ ፡ እንዲገድሉት ።
ለጊዜው ፡ አምጡና ፡ የተላከውን ፡ ሰው ፡
በእርግጥ ፡ መፈታቱን ፡ እሱም ፡ እንዲረዳ ፡
ከእስር ፡ ቤት ፡ አውጥቶ ፡ ፈትቶ ፡ ማሳየት ፡ ነው ።
አልገባም ፡ እንኳን ፡ ቢል ፡ በመጠራጠር ፡
ታመኻል ፡ እያሉ ፡ መንገር ፡ በምስጢር ፤
ተመርመርና ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ አታሎ ፡ አግብቶ ፡
ከሐኪሞቹ ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ ተስማምቶ ፡
በዚህ ፡ ካላለቀ ፡ ይህ ፡ የኛ ፡ ምክር ፡
ከወዴት ፡ ይገኛል ፡ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ምስጢር ፡
ይህ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ፡ በዚህ ፡ ይመከር ።

ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ እንደኔ ፡ አስተያየት ፡
እስቲ ፡ ሁላችሁም ፡ በዚህ ፡ ምከሩበት ።

ካለ ፡ በኋላ ፡ አንደኛው ፡ ተነሥቶ ፡ በምክሩ ፡ የተደሰተ ፡ መሆኑን ፡ ገለጸላቸው ።

እኔ ፡ ተጨንቄ ፡ የማወራው ፡ ሳጣ ፡
እንዴት ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ ጥሩ ፡ አሳብ ፡ መጣ ።
ጥሩ ፡ ነው ፡ አሳቡ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡
ያሁኑ ፡ ምክራችሁ ፡ ለኔ ፡ ተሰምቶኛል ፤
ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ምን ፡ መንገድ ፡ ይገኛል ።
ከመልክተኛው ፡ ጋር ፡ አሽከር ፡ ይላክና ፡
ለወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ትእዛዝ ፡ ይጻፍና ፤
ተፈቶ ፡ ይምጣና ፡ ሮማ ፡ ሲገባ ፡
ልትሄድ ፡ ነው ፡ ስንለው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡
እሱም ፡ ተደስቶ ፡ ሆዱኳን ፡ ሳይበባ ።
አምናለሁ ፡ በውነቱ ፡ የተማረ ፡ ነው ፤
ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንድትሄድ ፡ ስንለው ፤
ለጉዞውም ፡ ቢሆን ፡ ለማናቸውም ፡
እኔ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ እንደሚታከም ፤
በዚህ ፡ ይመከር ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡
ያለበለዚያማ ፡ ገመና ፡ ማውጣት ፡ ነው ።

መልክተኛው ፡ ይጠራል ፤ መልክተኛ ፡ ይገባና ፡ ዋና ፡ አማካሪው ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጠዋል ።

ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የተላከውን ፡ ቃል ፡
እኛም ፡ ተመልክተን ፡ ተማክረንበታል ፤
እስረኛው ፡ ይመለስ ፡ ይፈታ ፡ ከስር ፡
ይሂድ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ጥንቱ ፡ ክብር ፤

አንተም ፡ መልክተኛው ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ይዘህ ፡
ከተፈቻ ፡ ወዲያ ፡ እስረኛው ፡ ወንድምህ ፡
ለመንገዱም ፡ ቢሆን ፡ ለማናቸውም ፡
እንደ ፡ ሕክምና ፡ የሚጠቅም ፡ የለም ፤
ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ከዚህ ፡ እንዲታከም ፤

ብለው ፡ ዋናው ፡ አማካሪ ፡ ያሰናብቱታል ። መልክተኛውም ፡ ጀግናው ፡ ወደ ፡ ታሰረበት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሲሲል ፡ ይሄድና ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ይሰጠዋል ፤ የወህኒውም ፡ ሹም ፡ ተቀብሎ ፡ መልክተኛውን ፡ ይዞ ፡ ዘርዓይ ፡ ወዳለበት ፡ ክፍል ፡ ይሄድና ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ካጽናናው ፡ በኋላ ፡ ፈቶ ፡ ይለቀዋል ።

እንዴት ፡ ያለ ፡ ጀግና ፡ ጥሩ ፡ ዋስ ፡ አለህ ፤
አገሩን ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ ፡ አንተን ፡ አስፈታህ ።
ደፋሩ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወጣቱ ፡ ዘርዓይ ፡
መቼየት ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ዋስ ፡ አገኘህ ፡ ወይ ።
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዋስ ፡ ከወዴት ፡ ይገኛል ፤
ለዋስትና ፡ በቅቶ ፡ በዓለም ፡ ይጠራል ።
አንተ ፡ ግን ፡ በኛ ፡ አገር ፡ የሠራኸው ፡ ሥራ ፡
ይኖራል ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ሲያበራ ።
ላገራችሁና ፡ ለወገኖቻችሁ ፡
ያገራችሁን ፡ ክብር ፡ ዛሬ ፡ ፈጸማችሁ ።
የሠራኸውን ፡ ታሪክ ፡ ዝናህን ፡ ሰምቼ ፡
ልለቅህ ፡ ነበረ ፡ በነጻ ፡ ፈትቼ ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ቢሆን ፡ አንተን ፡ መሳይ ፡ ጀግና ፡
የትም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ዋስ ፡ አያጣምና ፤
ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ በዋስ ፡ ተፈታህ ፡

በል ፡ እስቲ ፡ በደኅና ፡ አገርህ ፡ ያግባህ ፤
ላገርህ ፡ ለወንዝህ ፡ ለክብርህ ፡ ያብቃህ ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ተመስገን ፡ አምላኬ ፡ ለዚህ ፡ ያበቃኸኝ ፤
ከዚህ ፡ ከወንድሜ ፡ በዓይን ፡ ያገናኘኸኝ ።
እኔ ፡ እንኳ ፡ ሐሳቤ ፡ ነበር ፡ ለመሞት ፡
በታሪክ ፡ ገባያ ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፡ ለፊት ።
እግዜር ፡ ይቅር ፡ ብሏት ፡ ኢትዮጵያን ፡
በኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ልያት ፡ አገሬን ።
ሰማህ ፡ ወይ ፡ ወንድሜ ፡ አንተም ፡ ዘበኛው ፡
አመሰግናለሁ ፡ አሁን ፡ ስላልከው ።
ለመልካም ፡ ምኞትህ ፡ ለመልካም ፡ አሳብህ ፡
አመሰግናለሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ።

ተባብለው ፡ ይለያዩና ፡ ዘርዓይ ፡ ጕዞውን ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ይቀጥላል ፤ ዘርዓይ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ለመመርመር ፡ ይገባል ፤ ሐኪሙ ፡ ምርመራውን ፡ ያደርጋል ፤ ምርመራውን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተውን ፡ ቃል ፡ ይናገራል ።

## ክፍል ፡ ፲፩ ።

ዶክተር ፤ ሰማህ ፡ ወይ ፡ ዘርዓይ ፡ ጥቂት ፡ አሞኻል ፡
ከመሄድህ ፡ በፊት ፡ መታከም ፡ ይሻላል ።

ዘርዓይ ፡ ደረስ ፤ ከስር ፡ ቤት ፡ ስወጣ ፡ በጣም ፡ ጤና ፡ ነኝ ፥
አሞኻል ፡ ብትለኝ ፡ እውነትም ፡ አይመስለኝ ፤
የበሽታዬን ፡ ስም ፡ እባክህ ፡ ንገረኝ ።

ዶክተር ፤ ቱቤርክሎዝ ፡ ሕመም ፡ ነው ፡ የዠመረህ ፥
ሕክምና ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ የሚጠቅምህ ፤

እንደ ፡ መረመርኩህ ፡ እኔ ፡ ካከምሁህ ፡
ጥርጣሬ ፡ አታድርግ ፡ እኔ ፡ እንደማድንህ ።

ዘርዓይ ፡ እንደ ፡ ተመከረበት ፡ ባለማወቁ ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ ይተኛና ፡ ድኖ ፡ በሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ወደ ፡ ውድ ፡ አገሩ ፡ ለመምጣት ፡ ሲጠባበቅ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፤ ሐምሌ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እሬጅና ፡ ኤሊና ፡ በሚባለው ፡ ሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ ዐረፈ ።

የዘርዓይ ፡ መጨረሻ ፡ ንግግር ፤ ሳያመኝ ፡ ገብቼ ፡ እንዲያው ፡ ሲያቀብጠኝ ፡
ሐኪም ፡ ቤት ፡ አግብተው ፡ በዘዴ ፡ ሊገድሉኝ ፡
ሆስፒታል ፡ ገብቼ ፡ ከመንገላታት ፡
ምነው ፡ የዚያን ፡ ዕለት ፡ በክብር ፡ ብሞት ።
በዘዴ ፡ መሞቴን ፡ ትውልድ ፡ አይርሳው ፤
በነጭ ፡ ወረቀት ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰው ።
ደኅና ፡ ሁኚ ፡ አገሬ ፡ ሞትኩ ፡ እንደ ፡ ናፈቅሁሽ ፤
እንደ ፡ ኰራሽ ፡ ኑሪ ፡ በዓለም ፡ እንደ ፡ ታወቅሽ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ የሚናፍቀውን ፡ የአንበሳውን ፡ የዘርዓይ ፡ ደረስን ፡ ሞት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ አዘነለት ።

ለክብር ፡ ለሽልማት ፡ የታሰበውን ፡
አስቀሩት ፡ በዘዴ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስን ።
የዚያን ፡ ዕለት ፡ ያልሞትከው ፡ አንበሳው ፡ ዘርዓይ
አንተም ፡ እንደ ፡ ሰዎች ፡ መሞትህ ፡ ነወይ ፤
በዘዴ ፡ መሞትህ ፡ ታውቋል ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡
የወንዶች ፡ ምልክት ፡ አንበሳው ፡ ዘርዓይ ።
ሞት ፡ ለማንም ፡ አይቀር ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ይሞታል ፥
አንተ ፡ የሠራኸው ፡ ያስመሰግንሃል ፤
ለኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ አርኣያ ፡ ሆነሃል ።

በሰው ፡ አደባባይ ፡ ጠላት ፡ የሚያስጨንቅ ፡
የአገሩን ፡ ክብር ፡ ሰይፍ ፡ መዞ ፡ የሚጠብቅ ።
በሰይፍ ፡ በጐራዴ ፡ ዐጭዶ ፡ የሚወቃው ፡
የጀግኖች ፡ ምልክት ፡ ዘርዓይ ፡ አንበሳው ፡
ሞተ ፡ ተቀበረ ፡ እንግዲህ ፡ በቃው ።
ኢትዮጵያውያን ፡ እንደ ት ፡ ተጉን ፡
አንበሳውን ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይን ፡ አጣን ።
ከዚያ ፡ መዓት ፡ ሲተርፍ ፡ ከስድስት ፡ ጥይት ፡
በሰይፍ ፡ ሲከላከል ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡
ደክሞት ፡ ወደቀ ፡ አሉ ፡ ዘርዓይ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ።
የሮማ ፡ ሆስፒታል ፡ ሬጅና ፡ ኤሊና ፡
በትግል ፡ ጣለችው ፡ አንበሳውን ፡ ጀግና ።
የታሰበለትስ ፡ ረዥም ፡ ነበረ ፡
እወጣ ፡ እወጣ ፡ ሲል ፡ ጀግናው ፡ ባጭር ፡ ቀረ ።
አገሩን ፡ ለማየት ፡ እንያ ፡ ሲናፍ ቅ ፡
ቀረ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ በሬጅና ፡ ሐይቅ ።
ሞት ፡ ለማንም ፡ አይቀር ፡ ታዟል ፡ ከላይ ፡
መልካም ፡ ስም ፡ ይኖራል ፡ ዘላለም ፡ በዓለም ፡ ላይ ።
ኢትዮጵያውያን ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡
መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠርተን ፡ ለአገራችን ፡
እንደ ፡ ዘርዓይ ፡ ደረስ ፡ መሞት ፡ አለብን ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ባሳተምሁበት ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ጌታቸው ፡ ዐወቀ ፡ በሐሳብ ፡ ስለ ፡ ረዱኝ ፡ ሳላመሰግናቸው ፡ አላልፍም ።

# አ ክ ተ ሮ ች ።

፩፤ የአስመራ ፡ አገረ ፡ ገዥ ።

፪፤ ዘርዓይ ፡ ደረስ ።

፫፤ የአስመራ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ መልክተኛ ።

፬፤ የአገረ ፡ ገዥው ፡ አማካሪ ።

፭፤ ሽማግሌዎች ።

፮፤ ጋዜጣ ፡ ሸያጭ ።

፯፤ ወታደሩ ።

፰፤ የሮማው ፡ የጦር ፡ መኰንን ።

፱፤ የሙሶሊኒ ፡ ፍርድ ።

SCHOOL OF ORIENTAL & AFRICAN STUDIES
LONDON

ከደራሲው ፡ ተዘጋጅተው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሚ
ታተሙ ፡ መጻሕፍቶች ።

፩ኛ ፡ (ይገዛልሽ ፡ ዕድሜ) ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ።

፪ኛ ፤ (የአጻጻፍ ፡ ዘዴ) ፡ ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ።

ዋጋው ፡ ፩ ፡ ብር ፡ ከ፳፭ ፡ ሳንቲም ።